# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ



# ብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ

## (ከ2017 እስከ 2020 በጀት ዓመት)

ሐምሌ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


አጭር መግለጫ ........ 3

ምስጋና ........ 4

1. መግቢያ ........ 5

2. የነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና ........ 6

2.1. ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሁኔታ ........ 6

2.2. የኢትዮጵያ ነባራዊ የኢኮኖሚ ሁኔታ ........ 8

2.3. የቅርብ ጊዜ የታክስ ገቢ አፈጻጸም ........ 13

2.4. የኢትዮጵያ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ንጽጽር ........ 19

2.5. በኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ የታክስ ገቢ አሰባሰብ ተግዳሮቶች ........ 22

3. የቅርብ ጊዜ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ........ 24

3.1. የቅርብ ጊዜ የፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ........ 25

3.2. በቅርብ ጊዜ በታክስ አስተዳደር የተከናወኑ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ........ 31

4. የብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ........ 36

4.1. የብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ ስልት ........ 38

4.2. የታክስ የፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያ ........ 40

4.3. የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ........ 48

4.4. ታክስ ያልሆኑ የገቢ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ........ 52

5. የስኬት ምክንያቶች እና የትግበራ ስጋቶች ........ 53

5.1. የስኬት ምክንያቶች ........ 53

5.2. የትግበራ ስጋቶች ........ 54

6. የስትራቴጂው ፍኖተ ካርታ፣ ክትትል እና ግምገማ ማዕቀፍ ........ 55

6.1. የስትራቴጂው ፍኖተ ካርታ ........ 55

6.2. የክትትል እና ግምገማ ማዕቀፍ ........ 59

6.3. ስትራተጂውን ለመተግበር የተቀረጸ አደረጃጀት ........ 60

7. ማጠቃለያ ........ 62

አባሪ ........ 65

# አጭር መግለጫ

| | |
|---|---|
| AfCFTA | የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጠና |
| AfDB | የአፍሪካ ልማት ባንክ |
| AYSCUDA | የጉምሩክ መረጃ ስርዓት |
| BEPS | ታክስ መሠረት መሸርሸር እና የትርፍ ስወራ |
| CSOs | የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች |
| eCMS | ኤሌክትሮኒክ የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት |
| FY | የበጀት ዓመት |
| IT | የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ |
| LTO | ከፍተኛ የግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ |
| MAT | የዝቅተኛ ታክስ አማራጭ |
| MEFF | የመካከለኛ ዘመን የማክሮ-ኢኮኖሚፊስካል ማዕቀፍ |
| MoF | የገንዘብ ሚኒስቴር |
| MoPD | የፕላንና ልማት ሚኒስቴር |
| MoR | የገቢዎች ሚኒስቴር |
| NBE | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ |
| NMTRS | ብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ |
| OECD | የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ድርጅት |
| SOEs | የመንግስት ልማት ድርጅጅቶች |
| SSA | ከሰሃራ በታች ያሉ አፍሪካሀገራት |
| TADAT | የታክስ አስተዳደር ጤናማነት ምዘና |
| WTO | የዓለም ንግድ ድርጅት |

# ምስጋና

ይህ ብሄራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ የተዘጋጀው ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከገቢዎች ሚኒስቴር እና ከጉምሩክ ኮሚሽን በተወጣጣ የባለሙያዎች ቡድን ሲሆን፤ ይህ የባለሙያዎች ቡድን የአለም ባንክ፣ የፊስካል ጥናት ኢንስቲትዩት (IFS/TaxDev) እና የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ገንቢ ድጋፍ አግኝተዋል።

የዓለም የገንዘብ ድርጅት ቡዱኑ ስትራቴጂውን ለማዘጋጀት ሂደት የመነሻ የሚያግዝ እቀውቀት ይኖረው ዘንድ በመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ ምንነት፣ መርሆች፣ ይዘት ወዘተ አውደ ጥናት በማዘጋጀት ሥልጠና የሰጠ ሲሆን፤ ስልጠናውም ስራውን ለመጀመር ጠቃሚ የነበረ ሲሆን ድርጅቱ በተዘጋጀው ረቂቅ ስትራቴጂ ሰነድ ላይ የሰጠን ገንቢ ግብዓት እናመሰግናለን። በተመሳሳይ የፊስካል ጥናት ኢንስቲትዩት (IFS/TaxDev)፣ የዓለም ባንክ እና የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (UNECA) ድጋፍ ወሳኝ የነበረ በመሆኑ ከፍተኛ ምስጋና ይገባቸዋል። በተለይም የፊስካል ጥናት ኢንስቲትዩት (IFS/TaxDev) የስትራቴጂው ሥራ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ መጨረሻ ድረስ የማይተካ እና ወሳኝ ሚና የነበረው በመሆኑ ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን። በመጨረሻም ስትራቴጂውን ለማዘጋጀት በተለያየ መንገድ ድጋፍ ላደረጉ የፌዴራል፣ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት፣ የከተማ አስተዳደሮች እና ሌሎች አካላት ላደረጉት ገንቢ አስተዋጽኦ እናመሰግናለን።

# 1. መግቢያ

የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ (MTRS) ለአንድ ኢኮኖሚ በተለይም በእድገት ላይ ለሚገኙና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው አገራት ለሚያወጡት የልማት ዕቅድ ውጤታማነት ቁልፍ ሚና አለው። በመሆኑም ከሚመለከታቸው ባለድሻ አካላት ጋር በተቀናጀ መልኩ የተዘጋጀ የገቢ ስትራቴጂ መንግሥት የሀገር ውስጥ የገቢ ዕምቅ አቅም አሟጦ በመሰብሰብ የፊስካል አቅም (fiscal space) እንዲኖረው በማድረግና የውጭ ዕርዳታ ላይ ያለውን ጥገኝነት በመቀነስ፣ የፖሊሲ ነጻነት በማጎናጸፍ ብሎም የፊስካል ዘላቂነትን በማረጋገጥ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማትን ለማፋጠን ያግዛል። ስትራቴጂው የገቢ አሰባሰብ ጥረቶችን በማጎልበት እና በማጠናከር የታክስ ፖሊሲንና የአስተዳደር ሪፎርሞችንና ማሻሻያዎችን ለመተግበር ይረዳል። በዚህም መንግስት ለህዝቡ የሚያቀርባቸውን መሰረታዊ አገልግሎቶች እና የመሰረተ ልማት በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ለማዳረስ እና የድህነትን ቅነሳ ጥረቶችን ለመደገፍ እንዲቻል የሚጠበቀውን ገቢ በዘላቂነት ለማመንጨት ያስችላል። ከዚህም በተጨማሪ ለታክስ ከፋዮች፣ ለልማት አጋሮች እና ለህዝቡ በታክስ ስርዓቱ ስለሚደረጉ የሪፎርሙ እና የማሻሻያ ስራዎች ከወዲሁ ግንዛቤ እና ግልጽነት በመፍጠር ለስኬቱ የበኩላቸው ሚና እንዲጫወቱ ያግዛል። ይህም እቅድ ማውጣትን፣ የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንትን እና የህዝብ ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችሉ ሁኔታ ያመቻቻል። በተጨማሪም በመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚ ፊስካል ማዕቀፍ የታቀደውን የመንግስት ገቢ እና የወጪ ዕቅድ የተጣጣመ እንዲሆን በማድረግ ሊፈጠር የሚችል የበጀት ጉድለት (budget deficit) እንዲቀንስ በማድረግ አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት እንዳይኖር ያደርጋል።

መንግስት ከ2017 እስከ 2020 በጀት ዓመት የሚተገበርና ከ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ጋር የተጣጣመ የመካከለኛ ብሔራዊ የገቢ ስትራቴጂ ነድፏል። ይህ ስትራቴጂ የታክስ ሥርዓቱን ለማዘመን እና ለግል ኢንቨስትመንቱ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የታለመ ሲሆን አጠቃላይ የታክስ ፖሊሲዎችን እና አስተዳደራዊ ሪፎርሞችን እና ማሻሻያዎችን ለመተግበር ያስችላል። በዚህም የአምራች ኢኮኖሚ ዘርፉን ብሎም የሃገሪቱን ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ተወዳዳሪነት ያጠናክራል። አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ሃብት አሰባሰብን በማሻሻል፣ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ ከፍ በማርደግ በ2016 በጀት ዓመት የነበረውን 6.3 በመቶ በስትራቴጂው የትግበራ ዘመን መጨረሻ ዓመት 13.2 በመቶ ለማድረስ ዕቅድ ተይዟል። .

በስትራቴጂው መሰረት በሚከናወኑ የታክስ ፖሊሲ እና የአስተዳደር ሪፎርሞችና ማሻሻያዎች በአፈጻጸም ሂደት ላይ ሊፈጠር የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት ጫና በማይፈጠር መልኩ ለመተግበር ታልሟል። የታክስ መሰረቱን ለማስፋት ብሎም ስርዓቱን በማዘመን በስትራቴጂው የተመለከቱ የአስተዳደር ሪፎርሞችን እና ማሻሻያዎችን ተግባራዊ በማድረግ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በ2.9 መቶኛ ለማሳደግ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን፤ በተመሳሳይ የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞችን እና ማሻሻያዎችን በመተግበር ተጨማሪ በ4 መቶኛ በማሳደግ በ2020 በጀት ዓመት የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 13.2 በመቶ ለማድረስ ዕቅድ ተይዟል።

ስትራቴጂውን ተግባራዊ ለማድረግና የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበትና የበኩላቸውን ድርሻ የሚወጡበት ግልጽ የሆነ ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀትንና የተቀናጀ ጥረትን ይጠይቃል። ይህንንም ለማሳካት ስትራቴጂው ዋና ዋና ባለድርሻ አካላትን በመለየት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በዝርዝር አመላክቷል። የገንዘብ ሚኒስቴር የስትራቴጂውን ትግበራ ያስተባብራል፤ ይመራል፤ ሂደቱን ይከታተላል እንዲሁም ይገመግማል።

# 2. የነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና


ብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂው በሀገር ውስጥ፣ በዓለም አቀፍ እና በቀጠናው ባለው ኢኮኖሚያዊ አውድ ላይ የተመሰረተ ነው።

## 2.1. ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሁኔታ

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና በዩክሬን እየተካሄደ ያለው ጦርነት የዓለም ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጥሯል። የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና ሀገራት የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የወሰዱት የእንቅስቃሴ ገደብ እርምጃ ዓለም አቀፍ የምርት አቅርቦት ሰንሰለቱን በእጅጉ እንዲስተጓጎል አድርጎታል። በዚህም እ.ኤ.አ. በ2020 ሁሉም የዓለም ሀገራት ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት መቀነስ አጋጥሟቸዋል (ከዚህ በታች ያለውን ሥዕል ይመልከቱ)። ይህም የአለም ኢኮኖሚ በ3 በመቶ የሚጠጋ፣ የአውሮፓ ህብረት አገራት 6.1 በመቶ፣ በሁሉም የበጸጉ አገራት 4.4 በመቶ፣ እና ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገራት 1.6 በመቶ ሊቀንስ ችሏል። መንግስታት በተለይ ያደጉ አገራት የወሰዱት ጥብቅ የመንቀሳቀስ ገደብ (lockdown) እርምጃ ለከፍተኛ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ አስተዋፅዖ አድርገዋል። ከሰሃራ

በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራት (SSA) የኢኮኖሚ ዕድገት መቀዛቀዝ ቢያጋጥማቸውም በሌሎች የዓለም ክፍሎች የታየውን ያህል አልነበረም።

**ምስል 2.1. ለተመረጡ የዓለም ክፍሎችች የዋጋ ንረትን ታሳቢ ያደረገ የሀገር ውስጥ ምርት (real GDP) ዕድገት እና ትንበያ (%) - እ.ኤ.አ. ከ2010 እስከ 2027**




*ማስታወሻ* ፡ ባለ ነጥብ መስመሮች የIMF ትንበያዎችን ያመላክታሉ።

*ምንጭ* ፡ የIMF የዓለም ኢኮኖሚ አውትሉክ መረጃ ቋት (2023)

በተጨማሪ እ.ኤ.አ. በ2022 የዩክሬን ጦርነት በዓለም ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። ይህም የኃይል አቅርቦት በማስተጓጎል የኑሮ ውድነቱ እንዲባባስ አድርጓል። በዚህም ወቅት የአለም ኢኮኖሚ በ3.2 በመቶ፣ የአውሮፓ ህብረት አባል ሃገራት በ2.2 በመቶ እና ከሳሀራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ ሀገራት በ3.7 በመቶ ብቻ ዕድገት አሳይተዋል። የዩክሬንን ጦርነት ተከትሎ የተከሰተው ዓለም አቀፍ የሸቀጦች ዋጋ መዋዠቅ ብሎም ጥብቅ የካፒታል (የገንዘብ) ፍሰት ቁጥጥር በተለያዩ የዓለማችን ክፍል ያለው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በአንጻራዊነት አዳክሞታል (IMF 2022 ከላይ ያለውን ምስል ይመልከቱ) ከሳሀራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ ሀገራት የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ትንበያ ከሌሎች የዓለማችን ክፍሎች ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ሲሆን፤ እ.ኤ.አ በ2023 በ3.7 በመቶ እና በ2024 ከ4 በመቶ በላይ እንደሚያድግ ይገመታል።

እ.ኤ.አ. በ2021 ሁሉም ሀገራት በሚባል ደረጃ ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ በፍጥነት በማገገም አንፃራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት በማሳየት፤ የዓለም ኢኮኖሚ የ6.0 በመቶ፣ ሁሉም ያደጉ ሃገራት የ5.2 በመቶ፣ እና ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራት የ4.7 በመቶ እድገት


አስመዝግበዋል፡፡ የኮቪድ-19 የእንቅስቃሴ ገደብ እርምጃዎችን ማላላት እና የክትባቱ ስርጭት በተለይ በበለጸጉ ሃገራት ለታየው የኢኮኖሚ ማገገም ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ በተለያዩ ሃገራት ላይ የተከሰተው የፋይናንስ እጥረት፣ በዩክሬን ጦርነት ማግስት የአቅርቦት ሰንሰለት መስተጓጎል እና የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ እድገት ደካማ መሆን ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራት ኢኮኖሚ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል (የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ 2023)፡፡

## 2.2. የኢትዮጵያ ነባራዊ የኢኮኖሚ ሁኔታ

ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በተለይ ከ1996 እስከ 2012 ዓ.ም ኢትዮጵያ ፈጣን የሚባል የኢኮኖሚ እድገት አስመዝግባለች፡፡ በዚህ ወቅት አመታዊ አማካይ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 10.3 በመቶ በማደግ በቀጣናው ፈጣን ኢኮኖሚ ካስመዘገቡ ሀገራት አንዷ ነበረች፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ዕድገት ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ተቀስቅሶ በነበርው ግጭት፣ በደቡብና ምስራቅ የአገሪቱ ክፍል በተከሰተው የዝናብ እጥረት እና ባስከተለው ድርቅ፣ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና የዩክሬን ጦርነት ምክንያት መቀዛቀዝ አሳይቷል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ተከትሎ በቀጠናው በሚገኙ ሀገራት ውስጥ የነበረውን አጠቃላይ የሃገር ዉስጥ ምርት እድገት ደካማ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በ2013 ዓ.ም ወደ 6 በመቶ በማሳየት በቀጠናው ከሚገኙ ሌሎች ሀገራት ጋር ሲነጻጸር ፈጣን ዕድገት ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ የዓለም የገንዘብ ድርጅት መረጃ እንደሚያመለክተው በቀጠናው የሚገኙ ሃገራት ኬንያንና ሩዋንዳን ጨምሮ በዚሁ ወቅት ማለትም እ.ኤ.አ. በ2020 አጠቃላይ የምርት መኮማተር (GDP contraction) አሳይተዋል፡፡ ነገር ግን እ.ኤ.አ. በ 2021 ሁሉም የቀጠናው አገራት በሚባል ደረጃ በአንፃራዊነት ፈጣን የሚባል አጠቃላይ የአገር ዉስጥ ምርት ዕድገት አስመዝግበዋል፡፡ በተመሳሳይ ምንም እንኳ የሰሜኑ ጦርነትና በሌሎች የሃገሪቱ አካባቢዎች የተከሰተው ድርቅ አሉታዊ ተፅዕኖ ቢፈጥርም ኢትዮጵያም ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገቧን ቀጥላለች፡፡


**ምስል 2.2. የዋጋ ንረትን ታሳቢ ያደረገ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት (%) እና የኢትዮጵያ እና የተመረጡ የየሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሃገራት እይታ - እ.ኤ.አ ከ2010 እስከ 2027**




*ማሳሰቢያ* ፡ ባለ ነጥብ መስመሮች የIMF ትንበያን ያመለክታሉ።
*ምንጭ* ፡ አለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (2023)

ግብርና በኢትዮጵያ ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት እና የስራ ዕድል ፈጠራ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው የኢኮኖሚ ዘርፍ ሲሆን በሌላ በኩል የኢንዱስትሪው ዘርፍ (ማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽን እና ኤሌክትሪክ ንዑስ ዘርፎችን ጨምሮ) አሁንም አነስተኛውን ድርሻ ይይዛል። በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ ከፋይናንስ ዘርፉ መስፋፋት ጋር ተያይዞ የአገልግሎት ዘርፉ እያደገ ሲመጣ የግብርና አስተዋፅኦ እየቀነሰ መጥቶ ነበር። በዚህም በ1995 የአገልግሎት ዘርፉ የግብርናውን ዘርፍ ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) የነበረውን የቀደምትነት ድርሻ ወስዶ ነበር። ይሁን እንጂ ከ1996 እስከ 2003 ዓ.ም የግብርናው ዘርፍ የቀዳሚነት ድርሻውን መልሶ ይዟል። ይህ ግብርና ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (በወቅቱ ባለው የገበያ ዋጋ) ድርሻ ከፍ ያለው የዘርፉ ምርታማነት መጨመር ሳይሆን የግብርና ምርቶች የዋጋ ጭማሪ ሊሆን እንደሚችል መረጃዎች ያሳያሉ። በዚህ ወቅት የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በአንፃራዊነት ጠንካራ እድገት በማሳየቱ በ2004 በጀት ዓመት ከነበረው ጠቅላላ ምርት 11.5 በመቶ ድርሻ በ2010 ወደ 28.8 በመቶ አድጓል። ነገርግን ባለፉት አምስት ዓመታት ዘርፉ መቀዛቀዝ አሳይቷል። የዓለም ባንክ መረጃ እንደሚያመላክተው ከስራ ዕድል ፈጠራ አንፃር ግብርናው ሁለት ሶስተኛው ገደማውን (64 በመቶ) የሰው ኃይል የሚቀጥር ሲሆን ኢንዱስትሪው 10 በመቶውን እና አገልግሎት ዘርፉ ደግሞ 26 በመቶ ያህሉን ይይዛሉ (የአለም ባንክ 2023)።

**ምስል 2.3. የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በኢኮኖሚ ዘርፎች በወቅቱ የገበያ ዋጋ (በ%) - 1992 እስከ 2014**





*ምንጭ፡- የፕላንና ልማት ሚኒስቴር*

በዚህ ወቅት ሀገሪቱ ባስመዘገበችው ፈጣንና አካታች የኢኮኖሚ ዕድገት ምክንያት በሀገሪቱ ከፍተኛ የድህነት ቅነሳ ታይቷል። የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ፍፁም የድህነት ጥምርታ (absolute poverty) እ.ኤ.አ. በ1995 ከነበረበት 69.2 በመቶ በ2015 ወደ 27 በመቶ ዝቅ ብሏል። ይሁን እንጂ የታየው የኢኮኖሚ ዕድገት የሀብት ክፍፍሉ ሚዛናዊ እንዳይሆን አድርጓል። በሀብት ክፍፍል ማሳያ (Gini coefficient) ሲለካ እ.ኤ.አ. በ1999 ከነበረበት 0.3 በ2015 ወደ 0.35 ዕድገት አሳይቷል (የአለም ባንክ፣ 2023)።

ሆኖም ኢኮኖሚው አሁንም ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ግሽበት፣ እያደገ የመጣ የመንግስት እዳ፣ የስራ አጥነት፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እና ደካማ የሆነ የውጭ ንግድን ጨምሮ ብዙ ፈተናዎች ተጋርጠውበታል። በ2014 ዓ/ም አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ከ27 በመቶ በላይ የነበረ ሲሆን የምግብ ግሽበት ደግሞ 32 በመቶ ገደማ ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም በሀገሪቱ ባለፉት አስር አመታት ውስጥ ከታየው የዋጋ ግሽበት ከፍተኛ ሀኖ ተመዝግቧል። በኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተከሰተው ድርቅ እና በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ተቀስቅሶ በነበረው ግጭት የአቅርቦት ሰንሰለቱን በመስተጓጎሉ ምክንያት የዋጋ ግሽበቱ እንዲባባስ አድርጓል።


**ምስል 2.4. ዓመታዊ የዋጋ ግሽበት በኢትዮጵያ (%) - ከ1996 እስከ 2015**




*ምንጭ ፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ*

በሌላ በኩል አጠቃላይ የመንግስት በጀት ሚዛን ስንመለከት ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት አንፃራዊ መረጋጋት አሳይቷል፡፡ ከ1996 እስከ 2003 ዓ/ም መጠነኛ ቅናሽ ያሳየ ቢሆንም ይህ አፈጻጸም ባለፉት ጥቂት ዓመታት የመንግስተ ገቢ እና ወጪ ባለመመጣጠኑ ምክንያት የሀገሪቱ የበጀት ሚዛን ጉድለቱ እየሰፋ መጥቷል፡፡ ለዚህም ከልማት አጋራ የሚገኘው ድጋፍ መቀዛቀዙ እና የሀገር ውስጥ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አንፃር ሲታይ መቀነሱ አስተቀዋፅኦ አድርጓል፡፡ በ1996 አጠቃላይ የመንግስት ወጪ ከሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ 22.9 በመቶ የነበረ ቢሆንም በ2014 ወደ 12.8 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ በዚሁ ጊዜ አጠቃላይ የመንግስት ገቢከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ 20.0 በመቶ የነበረው ወደ 8.5 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ አጠቃላይ የመንግስት በጀት ሚዛን በ2000ዎቹ መጀመሪያ ላይ አንጻራዊ መሻሻል አሳይቷል፡፡ የልማት አጋሮችን ድጋፍ ጨምሮ የበጀት ጉድለቱ በ1996 ከነበረው 2.9 በመቶ በ2001 ወደ 0.9 በመቶ ዝቅ ብሎ የነበረ ቢሆንም ከ2008 ጀምሮ ጉድለቱ ዳግም እያደገ በመምጣት በ2014 ከ4 በመቶ በላይ ደርሷል፡፡


**ምስል 2.5. የመንግስት የበጀት ሚዛን እና የመንግስት ዕዳ (ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በመቶኛ)**




*ምንጭ ፡ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የፕላንና ልማት ሚኒስቴር*

የዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት በሚያወጣው መደበኛ የሃገራት የዕድ ጫና ዳሰሳ መሰረት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የብድር ጫና ተጋላጭነት ምድብ ውስጥ ትካተታለች፡፡ ይሁን እንጂ ባለፉት አምስት ዓመታት በመንግስት በተወሰዱ የሪፎርም እና የማሻሻያ እርምጃዎች አጠቃላይ የመንግስት ዕዳ ላይ መጠነኛ ቅናሽ ታይቷል፡፡ በዚህም መሰረት በ2010 ዓ/ም ከነበረበት ከ60 በመቶ በላይ በ2013 ከ50 በመቶ በታች ሊወርድ ችሏል፡፡ ይህም ቅናሽ በውጪ ዕዳ ላይ ከፍተኛ ለውጥ አሳይቷል፡፡መንግስት ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሀገር በቀል የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም I (HGER I) የተተገበሩ እርምጃዎች በተለይም ከፍተኛ የወለድ ምጣኔ ያላቸው የንግድ ብድር (commercial loans) ማስቀረትለታየው የውጤት መሻሻል አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

**ምስል 2.6. የመንግስት ዕዳ ክፍያ ጫና (ድርሻ በ % የከታክስ ገቢ የውጭ ዕርዳታን ሳይጨምር) ከ2006 እስከ 2013 ዓ.ም.**




*ምንጭ ፡- የገንዘብ ሚኒስቴር የታክስ ፖሊሲ መምሪያ*

ከላይ በምስሉ እንደሚታየው የኢትዮጵያ የዕዳ ክፍያ ጫና ከአጠቃላይ የታክስ ገቢ አንጻር ሲታይ (debt service) በ2006 ዓ/ም ከነበረው የ8.8 በመቶ በ2013 ወደ 21.2 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ ይህ የመንግስት የዕዳ ክፍያ አጠቃላይ የመንግስት ወጪን በመጨመር የበጀት ጉድለቱ እዲሰፋ ምክንያት ሆኗል፡፡


## 2.3. የቅርብ ጊዜ የታክስ ገቢ አፈጻጸም

የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በየዓመቱ በተከታታይ እየቀነሰ በመምጣት በ2007 ዓ/ም ከነበረበት የ12.4 በመቶ ድርሻ በ2015 ወደ 6.8 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ መንግሰት የታክስ ገቢ ዕምቅ አቅም አሟጦ ለመሰብሰብ እንዲቻል ለዘርፉ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት መሰረት በታክስ ፖሊሲ እና በታክስ ህጎች በርካታ የሪፎርም እና የማሻሻያ ስራዎች የተከናወኑ ቢሆንም የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ የነበረውን ድርሻ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ይህም ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አንፃር የታክስ ገቢ ዕድገት ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ጥምርታ ሁሉም የታክስ ዓይነቶች በሚባል ሁኔታ ቅናሽ አሳይቷል፡፡ ይህ የታክስ አሰባሰብ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሀገራት መሰብሰብ ከሚጠበቅባቸው ዝቅተኛ 15 በመቶ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ አንፃር በጣም ዝቅያለ ነው፡፡ ይህንን ዝቅተኛ እና በየዓመቱ በተከታታይ የታክስ ገቢ አሰባሰብ ለመቀልበስ እና የኢኮኖሚ

ልማት ለማፋጠን ሀገሪቱ ማመንጨት የምትችለውን ዕምቅ የገቢ ዓቅም አሟጦ በመሰብሰብ የታክስ ገቢ ለማሳደግ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት ይጠይቃል።

ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ ያለው የታክስ አሰባሰብ መረጃ እንደሚያመለክተው በ2014 ዓ/ም የሀገር ውስጥ ቀጥታ ታክስ ከአጠቃላይ ታክስ ገቢ 45 በመቶ በመያዝ ከፍተኛው ድርሻ ያለው ሲሆን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ 27.6 በመቶ እና የሀገር ውስጥ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች 27.5 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። ከሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚሰበሰበው የታክስ ገቢ ባለፉት ስምንት ዓመታት ውስጥ በወቅቱ ባለው የገበያ ዋጋ (nominal price) ከዓመት ዓመት ጭማሪ አሳይቷል። በተለይም የአገር ውስጥ ቀጥታ ታክሶች ከጠቅላላ የታክስ ገቢ ውስጥ ያለው ድርሻ 9 በመቶ ጨምሯል። በአንፃሩ የሀገር ውስጥ ቀጥተኛ ያልሆነ እና የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከአጠቃላይ የታክስ ገቢ ያላቸው ድርሻ ቀንሷል።

## ምስል 2.7 የኢትዮጵያ አጠቃላይ የታክስ ስብጥር (ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት) - ከ2007 እስከ 2015 ዓ.ም





*ምንጭ- የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የታክስ ፖሊሲ መምሪያ ስሌት*

ከ2007 እስከ 2015 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የነበረው ጥምርታ በተከታታይ ዓመታት እየቀነሰ መጥቷል። በተለይም የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ አፈጻጸም በከፍተኛ ደረጃ ቅናሽ አሳይተዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብቻ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የነበረው ድርሻ በ2.43 በመቶ ሲቀንስ፣ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ በ1.05 በመቶ እንዲሁም የንግድ ስራ ገቢ ግብር

በ0.72 በመቶ ሲቀንስ አጠቃላይ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በ4.2 በመቶ ቀንሷል።

**ምስል 2.8. የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የነበረው ድርሻ ለውጥ (በ2007 እና በ2015 መካከል)**





*ማሳሰቢያ፡- የትርፍ ገቢ ግብር ማለት በድርጅት እና ያልተደራጁ ንግዶች የገቢ ግብርን ይመለከታል። የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ የጉምሩክ ቀረጥ፣ የሱር ታክስ፣ የኤክሳይዝ ታክስ የሚየካትት ነው። ሌሎች ቀጥታ የሆኑ ታክሶች የኪራይ ገቢ ግብር፣ የትርፍ ድርሻ፣ የካፒታል ትርፍ፣ ሮያሊቲ፣ የገቢ ንግድ ላይ የሚጣል ዊዝሆልዲንግ፣ የወለድ ገቢ ታክስ፣ የግብርና ታክስ እና የከተማ የመሬት ታክስ የሚያጠቃልል ነው።*

*ምንጭ፡- በገንዘብ ሚኒስቴር የታክስፖሊሲ መምሪያ*

## 2.3.1. የሀገር ውስጥ ቀጥታ ታክሶች

የንግድ ሥራ የገቢ ግብር ቀጥታ ከሆኑ ታክሶች ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የደመወዝ/ምንዳ ገቢ ግብር ይከተላል። በአንጻሩ ከሌሎች ቀጥታ ታክሶች ማለትም የወለድ ገቢ፣ የሮያሊቲ፣ የዲቪደንድ እና የካፒታል ትርፍ የሚሰበሰበው ገቢ ዝቅተኛ ነው። በ2014 በጀት ዓመት የተሰበሰበ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ቀጥተኛ የታክስ ገቢ በብር 213 ቢሊዮን ሲሆን፤ ይህም ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የነበረው ጥምርታ 3.5 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። የንግድ ስራ ገቢ ግብር ከጠቅላላው ቀጥታ ታክስ ገቢ 47 በመቶ (በብር 106.7 ቢሊዮን) ድርሻ የሚይዝ ሲሆንይህም ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 1.6 በመቶ ነው። በሌላ በኩል ከደመወዝ/ምንዳ የሚሰበሰብ ገቢ 39 በመቶ (በብር 83 ቢሊዮን) ድርሻ የሚይዝ ሲሆን፤ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 1.3 በመቶ ነው። ሌሎች ቀጥታ ታክሶች በድምሩ ከ14 በመቶ ያነሰ ድርሻ ያላቸው መሆኑን መረጃው ያመላክታል።

**ምስል 2.9. የሀገር ውስጥ የታክስ አሰባሰብ በአይነት (በቢሊዮን ብር) 2007 እስከ 2015 ዓ.ም)**




*ምንጭ ፡- በገንዘብ ሚኒስቴር የታክስ ፖሊሲ መምሪያ ስሌት*

## 2.3.2. የሀገር ውስጥ ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች

የተጨማሪ እሴት ታክስ ከአገር ውስጥ ምርቶች እና አገልግሎቶች ከሚሰበሰበው ቀጥታ ካልሆኑ የታክስ ገቢዎች ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል። ከዚህ የታክስ ምንጭ በ2014 በጀት ዓመት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች ገቢ ውስጥ ከ70 በመቶ (ብር 92 ቢሊዮን) በላይ ሲሆን፤ ይህም ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 1.5 በመቶ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።


ከተጨማሪ እሴት ታክስ በመቀጠል በሁለተኛ ደረጃ የሚገኘ ከኤክሳይዝ ታክስ የሚሰበሰብ ገቢ ሲሆን፤ በ2014 በጀት ዓመት ብር 28.8 ቢሊዮን ወይም ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች ገቢ 22 በመቶ ይይዛል። ይህም ከኤክሳይዝ ታክስ የሚሰበሰብ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ከ0.5 በመቶ በታች ነው። የኤክሳይዝ ታክስ ገቢ በ2013 ከፍተኛ አፈጻጸም በማሳየት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች የነበረውን ድርሻ በከፍኛ መጠን ጭማሪ በማሳየት በ2012 ከነበረበት ብር 13.3 ቢሊዮን በ2013 በ78 በመቶ በማደግ ወደ ብር 23.6 ቢሊዮን ከፍ ብሏል። ይህ የ78 በመቶ ዕድገት በወቅቱ የገበያ ዋጋ ሲሆን የዋጋ ግሽበትን ከግምት ውስጥ በማስገባት በእውነተኛ ዋጋ የታክሱ ገቢ በ40 በመቶ ዕድገት የተመዘገበ ሲሆን ለዚህም በ2013 ዓ/ም የተደረገ የኤክሳይዝ ታክስ ሪፎርም ከፍተኛ ሚና ስለማበርከቱ መረዳት ይቻላል። ሌሎች ቀጥታ

ያልሆኑ ታክሶች በድምር ቀጥታ ከልሆኑ የሀገር ውስጥ ታክሶች ውስጥ ከ8 በመቶ በታች ድርሻ ወይም ብር 9.8 ቢሊዮን ነው።

### 2.3.3. የጉምሩክ ቀረጥና ታክሶች

በ2013 በጀት ዓመት ተከስቶ የነበረው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ገቢ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ጫና አሳድሯል። በዚህም አፈጻጸሙ ከ2012 በጀት ዓመት አንጻር ሲታይ ከዚህ ምንጭ የተሰበሰበ ገቢ በወቅቱ የገበያ ዋጋ 6 በመቶ ጭማሪ ያሳየ ሲሆን የዋጋ ንረትን ታሳቢ ያደረገ (real growth) የ16.5 በመቶ ቅናሽ አሳይቷል። ከዚህ የታክስ ምንጭ የተሰበሰበ ገቢ ከ2013 በጀት ዓመት አንጻር ሲታይ በ2014 የ23 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከተሰበሰበው የታክስ ገቢ ውስጥ የጉምሩክ ቀረጥ እና የሱር ታክስ ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው ሲሆን፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ በሁለተኛ ደረጃ ይከተላል።

ምስል 2.10. የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ስብጥር (በቢሊዮን ብር) ከ2007 እስከ 2015





*ምንጭ ፦ በገንዘብ ሚኒስቴርየታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት*

### 2.3.4. የታክስ ገቢ አሰባሰብ በቅርንጫፍ

የገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ተገዥነትን ለማሻሻል እንዲቻል ዓመታዊ የሽያጭ መጠን መሰረት በማድረግ በመላ ሀገራችን በየደረጃው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በማቋቋም እንደሚሰራ ይታወቃል። ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባደረገው የመልሶ ማዋቀር ስራ ከፍተኛ ታክስ ከፋዮች ጽ/ቤት፤ የመካከለኛ ታክስ ከፋዮች ጽ/ቤት እና አነስተኛ ታክስ ከፋዮች ጽ/ቤት በመክፈት ታክስ ከፋዮች የተሻለ አገልግሎት የሚያገኙበት አሰራር መሰረት በማድረግ ገቢ እየሰበሰበ ይገኛል። እነዚህ ቅ/ጽ/ቤቶች በፌዴራል ደረጃ በገቢ አሰባሰብ ሂደት ውስጥ ቁልፍ ሚና እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በ2010 በጀት ዓመት ከተሰበሰበው ጠቅላላ የፌዴራል የታክስ ገቢ ውስጥ ከፍተኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት 73.9 በመቶን ድርሻ የነበረው ሲሆን፤ የመካከለኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት እና አነስተኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በቀደም ተከተል 0.1 በመቶ እና 26.9 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። ይህ አፈጻጸም በ2015 በጀት ዓመት የከፍተኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ድርሻ በተወሰነ መጠን ዝቅ በማለት 67.4 በመቶ የነበረ ሲሆን፤ መካከለኛ እና አነስተኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች በቅደም ተከተል የ14.0 በመቶ እና የ18.6 በመቶ ድርሻ እንደነበራቸው መረጃው ያመለክታል። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው የከፍተኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከጠቅላላ የፌዴራል መንግስት ታክስ ገቢ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ እንደሆነ ነው። ይህም ለታክስ ከፋዩ የሚመጥን አደረጃጀት በመፍጠር የተሻለ የታክስ አስተዳደር አገልግሎት በመስጠት የታክስ ተገዥነት በማሻሻል በኩል የራሱን አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል።


ምስል 2.11. የፌዴራል መንግስት ታክስ አሰባሰብ በቅ/ጽ/ቤት (በ%) - ከ2010 እስከ 2015 በጀት ዓመት




*ማስታወሻ- እ.ኤ.አ የ2022/23 የታክስ ስብስብ የ11 ወራት ብቻ ነው (የሰኔ 2023 ሳይጨምር)።*
*ምንጭ- የገቢዎች ሚኒስቴር*

በፌዴራል መንግስት ደረጃ ከፍተኛ ድርሻ ያለው የታክስ ገቢ የሚሰበሰበው ከከፍተኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ሌሎች የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ ከነዚህ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ሌሎች የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች በ2010 በጀት ዓመት ከከፍተኛ ቅ/ጽ/ቤት ከተሰበሰበው ጠቅላላ የታክስ ገቢ ውስጥ 49 በመቶ ድርሻ ያላቸው ሲሆን፤ ቀሪውን 51 በመቶ ከግል ዘርፉ የተሰበሰበ መሆኑ መረጃው ያመለክታል፡፡ ይህ ድርሻ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለውጥ እያሳየ ሲሆን፤ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ሌሎች የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች 42.6 በመቶ እና የግል ድርጅቶች 57.4 በመቶ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

**ምስል 2.12. የከፍተኛ ታክስ ከፋዮች ቅጽ/ቤት የታክስ አሰባሰብ በዘርፍ - ከ2010 እስከ 2015 በጀት ዓመት**





*ማስታወሻ* ፡ የ2015 የታክስ አሰባሰብየ11 ወራት ብቻ ነው (የሰኔ 2015 ሳይጨምር)፡፡
*ምንጭ*- የገቢዎች ሚኒስቴር

## 2.4. በሀገራት መካከል ንጽጽር፡- የኢትዮጵያ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ንጽጽር

የኢትዮጵያ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ የማህበራዊ ዋስትና መዋጮን ሳይጨምር ከሰሃራ በታች ካሉት የአፍሪካ አገሮች አማካኝ በንጽጽር ሲታይ በእጅጉ ዝቅተኛ ሲሆን፤ ከሌሎች በተለየ መልኩ ኢኮኖሚው እያደገ በሄደ ቁጥር የታክስ ገቢ አፈጻጸሙ በየዓመቱ እየቀነሰ የሚሄድ ሆኖ ይታያል (ስዕል 2.13ን ይመልከቱ)፡፡


ምስል 2.13. የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በመቶኛ (ከነፍስ ወከፍ ገቢ) በንጽጽር፤




ምንጭ፡- በUNU-WIDER የመንግስት የገቢ መረጃ ላይ የተመሰረተ የፊስካል ጥናት ኢኒስቲትዩት ተቋም ትንተና፡፡

የኢትዮጵያ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በ2014 በጀት ዓመት የነበረው ድርሻ 6.8 በመቶ ሲሆን፤ ይህም እንደ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ ኮንጎ ሪፐብሊክ እና ሶማሊያ ከመሳሰሉ ሀገራት በመቀጠል የሚገኝ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል (ቀጥሎ ያለውን ምስል ይመልከቱ)፡፡ በሌላ በኩል እንደ ኬንያ፣ ኡጋንዳ እና ሩዋንዳ የመሳሰሉ ጎረቤት ሀገራት የታክስ ገቢ ከየሀገራቱ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ አንፃር ሲታይ የኢትዮጵያ በአማካይ ከግማሽ በታች መሆኑን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ2020 የኬንያ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ 14 በመቶ የነበረ ሲሆን፤ በተመሳሳይ ጊዜ የኢትዮጵያ 8.3 በመቶ መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡


**ምስል 2.14. እ.ኤ.አ በ2020 ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሳሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ ሀገራት የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ**




*ማሳሰቢያ፦ የኢትዮጵያ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ መረጃ የ2020/21 ነው፡፡*
*ምንጭ፦ UNU-WIDER የመንግስት የገቢ መረጃ፡፡*

ከታች በምስሉ ላይ እንደተመለከተው በታክስ ዓይነት ስብጥር የኢትዮጵያ የታክስ ገቢ ከአፍሪካ እና ሌሎች አህጉራት የሚገኙ ሀገራት የተለየ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም ከመቀጠር የሚገኝ ታክስን ሳይጨምር ከትርፍ ገቢ ግብር እና ከካፒታል ትርፍ በድምሩ የሚገኝ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 2.5 በመቶ ብቻ ሲሆን፤ የአፍሪካ አህጉር በአማካይ 6.2 በመቶ፣ የኤሲያ ፓስፊክ 7.7 በመቶ እና የላቲን አሜሪካ እና ካሪቢያን 5.9 በመቶ ነው፡፡ በተመሳሳይ ከሌሎች ሀገራት በንጽጽር ሲታይ ኢትዮጵያ ከሀገር ውስጥ ኤክሳይዝ ታክስ እና ሌሎች ቀጥታ ያልሆኑ የሀገር ውስጥ ታክሶች የምታገኘው የታክስ ገቢ ያነሰ ነው፡፡ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ገቢ አሰባሰብ ከሌሎች ሀገራት አፈጻጸም ተመሳሳይ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡

ምስል 2.15. የታክስ ገቢ አሰባሰብ በታክስ ዓይነት (ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በ%) እ.ኤ.አ በ2020




*ማሳሰቢያ* ፡ ለLAC እና እስያ-ፓሲፊክ ቁጥሮቹ አማካዩን ይወክላሉ፣ እና ጢሙ አማካኙን ያሳያል።
*ምንጭ* ፡ UNU -WIDER የመንግስት የገቢ መረጃ።

## 2.5. በኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ የታክስ ገቢ አሰባሰብ ተግዳሮቶች

### 2.5.1. የኢኮኖሚው መዋቅር

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከፍተኛ የታክስ ገቢ ያስገኛሉ የሚባሉ የአገልግሎት እና የኢንዱስትሪ የኢኮኖሚ ዘርፎች ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ ከፍ እያለ የመጣ ቢሆንም የታክስ ገቢ ከማመንጨት አኳያ ብዙም ያልሆነው የግብርና ዘርፍ ድርሻ ከፍተኛ ሆኖ ቀጥሏል። የግብርናው የኢኮኖሚ ዘርፍ በ2014 በጀት ዓመት ከ39 በመቶ በላይ የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ የነበረው ሲሆን፤ በተመሳሳይ ዓመት የአገልግሎት እና የኢንዱስትሪ ዘርፎች በቀደም ተከተል የ38 እና የ24 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። በአንፃሩ የሥራ ዕድል ከመፍጠር ረገድ የግብርናው ዘርፍ ከፍተኛውን መያዙን የቀጠለ ሲሆን፤ይህም እ.ኤ.አ በ2021 በኢትዮጵያ 64 በመቶ፣ በኬንያ 33 በመቶ እና ሩዋንዳ 55 በመቶ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ (ዓለም ባንክ፣ 2023)። የግብርናው ዘርፍ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ድርሻ ለመረዳት ዘርፉ ለአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያበረከተው የእሴት ጭማሪ ከሌሎች የአፍሪካ ኢኮኖሚዎች ጋር ማነፃፀር አስፈላጊ ይሆናል። በዚህም የግብርናው ክፍለ-ኢኮኖሚ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ እ.ኤ.አ በ2020/21 በኢትዮጵያ ከ37.57 በመቶ በላይ ሲሆን፤ በአንጻሩ የሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ከ30 በመቶ በታች ነው (ለምሳሌ በዛምቢያ 3፣ ሴኔጋል 15፣ ካሜሩን 17፣ ኬንያ 22፣ ማላዊ 23፣ ኡጋንዳ 8፣ ሩዋንዳ 24 እና ታንዛኒያ 26 በመቶ ነው) (የዓለም ባንክ፣ 2022)።

ግብርና ከፍተኛ ድርሻ በሚይዝበት ኢኮኖሚ ውስጥ የታክስ ገቢ በሚፈለገው ደረጃ ለመሰብሰብ የሚደረግ ጥረት ፈታኝ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ለዚህም የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ከኢ-መደበኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ቁርኝት አለው፡፡ በኢትዮጵያ ይህ ክፍለ ኢኮኖሚ 34 በመቶ ድርሻ ያለው ኢ-መደበኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ታክሎበት ለዝቅተኛ የታክስ አሰባሰብ የራሱ ሚና እንደሚጫወት ጥናቶች ያመላክታሉ(Besley and Persson, 2014; Kibret, 2016፣ McNabb et al 2021)፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የግብርና እና የኢ-መደበኛ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በአመዛኙ ከታክስ መረብ ውጭ የሚከናወኑ በመሆናቸው፤ እንዲሁም እነዚህን ወደ ታክስ መረቡ በማስገባት ሊገኝ ከሚችለው ገቢ አንፃር ከፍተኛ የታክስ አስተዳደር ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ ነው፡፡

### 2.5.2. ዝቅተኛ የታክስ አስተዳደር አቅም

መንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓቱን ለማሻሻል በርካታ ጥረቶች ያደረገ ቢሆንም፤ የታክስ አስተዳደር ጤናማነት የዳሰሳ ምዘና (TADAT)[1] ሪፖርት በሁሉም መስፈርቶች በሚባል ደረጃ በአማካይ ውጤቱ ዝቅተኛ ዲ(D) መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም በብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂው የታቀዱትን የተለያዩ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች በመተግበር በታክስ ገቢ አሰባሰቡ የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት የሚደረገውን ጥረት አዳጋች ሊያደርገው ይችላል፡፡ ብዙ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው እና በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገራት የታክስ ፖሊሲ በትክክል በመቅረፅ ተገቢውን የታክስ ገቢ ከመሰብሰብ አንፃር ውጤታማ የማይሆኑበት ምክንያት ፖሊሲዎችን በትክክል ለመተግበር የሚያስችል የታክስ አስተዳደር ስርዓት ስለማይኖራቸው ነው (Vehorn, 1997)፡፡

### 2.5.3. ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት


ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት በታክስ አሰባሰቡ እንደ ታክስ ዓይነቱ ሚና ሊኖረው ይችላል፡፡ ቀጥታ የሆኑ ታክሶች ከዋጋ ግሽበት ጋር አብሮ የሚያድጉ ስላልሆኑ እና ወጪን በማናር የትርፋማነትን መጠን ሊቀንሱ የሚችሉ በመሆናቸው ከነዚህ የታክስ ምንጮች ሊገኝ የሚችል ገቢ ሊቀንስ የሚችል ሲሆን፤ በአንፃሩ ቀጥታ ካሆኑ ታክስች ሊገኝ የሚችለው ገቢ በዋጋ ግሽበቱ መጠን ከፍ ሊል ይችላል፡፡

[1] በታክስ አስተዳደር ጤናማነት ምዘና (TADAT) መሰረት የደረጃ ውጤቱ ከ4 የሚመዘን ሲሆን ዲ (D) 1 እስከ 2 ነገር ግን 2ን ሳይጨምር፣ ሲ(C) ከ2 እስከ 3 ነገር ግን 3ን ሳይጨምር፣ ቢ(B) ከ3 እስከ 4 ነግር ግን 4 ሳይጨምር እና ኤ(A) 4 ነው፡፡

# 3. የቅርብ ጊዜ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች

በብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ የትግበራ ጊዜ መንግስት የፊስካል ፖሊሲውን በማጥበቅ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ በማስፈን እና የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለማስቀጠል ጥረት ያደርጋል፡፡ ስለሆነም የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች በመተግበር የሀገር ውስጥ ሃብትን በማሳደግ የፌደራል መንግስት በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት ብር 0.8 ትሪሊየን በ2020 በጀት ዓመት ብር 1.3 ትሪሊየን ወጪን መሸፈን ይጠበቃል (ከዚህ በታች ያለውን ምስል ይመልከቱ)፡፡

**ምስል 3.1. የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚ ፊስካል ማዕቀፍ የፌዴራል መንግሥት ወጪ ዕቅድ**




*ማብራሪያ፥ ከላይ የተቀመጠው አሃዝ (የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ከመደረጉ በፊት ስለነበር) የተቀመጡት አሃዞች በቅርብ የሚደረገውን የበጀት ማሻሻያ ታሳቢ ያለደረገ ነው፡፡*
*ምንጭ ፡ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የፊስካል ፖሊሲ መምሪያ*

## 3.1. የቅርብ ጊዜ የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች

የገንዘብ ሚኒስቴር ባለፉት ስድስት ዓመታት የተለያዩ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ ህግ ሪፎሞች እና ማሻሻያዎች አድርጓል፡፡ እነዚህ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች በመንግስት አስፈፃሚ አካላት በአዋጅ የፊስካ እና የታክስ ፖሊሲ ሀሳብ የማመንጨት ስልጣን መሰረት በገንዘብ ሚኒስቴር አመንጪነት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የተከናወኑ ሲሆኑ፤ ቁልፍ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 3.1.1. የድንበር ፍራንኮ-ቫሉታ ቀረጥና ታክስ ነጻ

በድንበር አካባቢ ያለውን የንግድ ልውውጥ ለማሳለጥ እና ህብረተሰቡ ኮትሮባንድን ከመከላከል አንጻር የበኩሉን ድርሻ እንዲጫወት ለማድረግ መንግስት በተመረጡ የድንበር አካባቢዎች የፍራንኮ-ቫሉታ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ግብይት እንዲፈቀድ አድርጎ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን፤ ዓላማውም የመብቱ ተጠቃሚዎች በራሳቸው የውጭ ምንዛሪ በመጠቀም በህጉ የተፈቀዱ ዕቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት መጠቀም እንዲችሉ ነው፡፡ ለዚሁ ዓላማ ሲባል መንግስት በየዓመቱ በአማካይ ከብር 4 ቢሊዮን በላይ ገቢ ሳይሰበሰብ የቀረሰ ሲሆን፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ስርዓቱ ለጉምሩክ ኮሚሽን አስተዳደር ፈታኝ ከመሆኑ በተጨማሪየፍትሐዊነት ችግር ያለበት እና ህብረተሰቡን በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ ሳያደርግ የጥቂት ህገ-ወጦች መጠቀሚያ ወይም የኮትሮባንድ ምንጭ መሆኑ በጥናት ተረጋግጧል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው በህጉ በተደነገገው መሰረት የክልል፣ የከተማ አስተዳደሮች እና የሚመለከታቸው የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በመተባበር ተግባራዊ ባለመደረጉ ነው፡፡ ስርዓቱ በነዚህ የድንበር አካባቢዎች ለህገ ወጥ ንግድ መስስፋፋት ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ በየጊዜው ከተለያዩ አካባቢዎች ተመሳሳይ ጥያቄዎች እንዲነሱ በማድረግ የሀገሪቱን አጠቃላይ የንግድ ስርዓት አደጋ ውስጥ በማስገባት የገቢ አሰባሰብ ላይ አላስፈላጊ ጫና ፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ በተመሳሳይ ሁኔታ ከሚገኙ መብቱ ባልተሰጣቸው አከባቢዎች ተመሳሳይ ዕድል እንዲሰጣቸው ጥያቄ ሲቀረቡ እና የቀረቡ ጥያቄዎች አውንታዊ ምላሽ ሳያገኙ ሲቀሩ የፍትሃዊነት ጥያቄ አንዳለበት ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑምእነዚህን ጉዳዮች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ስርዓቱበ2010 ዓ.ም እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡

### 3.1.2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ

ከፍተኛ ዋጋ ግሽበት እና የብር የመግዛት አቅም መዳከም ቢኖርም ለተጨማሪ እሴት ታክስ የግዴታ የመመዝገቢያ ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ብር 500 ሚሊዮን ማስተካከያ ሳይደረግበት ለበርካታ ዓመታት ቆይቷል፡፡ ይህ አነስተኛ ገቢ ያላቸውታክስ ከፋዮች ወደ ተጨማሪ እሴት ታክስ ስርዓት እንዲገቡ በማድረግ ለታክስ ሰብሳቢ ባለስልጣኑ ታክስ የመሰብሰብ አስተዳደራዊ ወጪዎችን እና ለታክስ ከፋዩ የታክስ ተገዢነት ወጪዎችን እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ የገንዘብ ሚኒስቴር ይህንን በመገንዘብ የተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገቢያ መጠንን በ2010 ዓ.ም ከ0.5 ሚሊዮን ወደ ብር 1 ሚሊየን ከፍ እንዲል በማድረግ እንዲሻሻል አድርጓል (ሰርኩላር T/K/Q/5/161)፡፡

በተጨማሪም በ2011 የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ የተፀደረገ ሲሆን፤ ይህም የተጨማሪ እሴት ታክስ ዊዝሆልዲንግ ማሻሻልን የሚጨምር ሲሆን፤የታክስ ወኪሎች በግዥቸው ላይ የሚከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ 100 በመቶ በመያዝ ለገቢዎች ሚኒስቴር ማስተላለፍ ይጠበቅባቸው የነበረው 50 በመቶ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህም የታክስ ወኪሎቹ በግዥያቸው ላይ የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ 50 በመቶ ብቻ እንዲይዙ፣ አቅራቢዎች ደግሞ ቀሪውን 50 በመቶ በመያዝ ለገቢዎች ሚኒስቴር እንዲያስተላልፉ ያስገድዳል፡፡

### 3.1.3. የኤክሳይስ ታክስ ሪፎርም እና ማሻሻያዎች

ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ መሰረታዊ የሚባል ማሻሻያ ሳይደረግበት በስራ ላይ የቆየውን የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 307/1995) በመተካት የኤክሳይስ ታክስ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1186/2012) ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ይህ ማሻሻያ የተለያዩ ለውጦችን ያካተተ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል በአገር ውስጥ የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች የታክስ መሰረት ከማምረቻ ወጪ ወደ ፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ መቀየሩ፣ የቁርጥ መጣኔ መተግበሩ፣ መሰረታዊ የሚባሉ ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ እንዳይጣልባቸው መደረጉን እና አዳዲስ ከዚህ በፊት የኤክሳይዝ ታክስ ሲጣልባቸው ያልነበሩ ምርቶች እና አገልግሎቶች የኤክሳይዝ ታክስ እንዲጣልባቸው መደረጉ ወዘተ ናቸው፡፡ ማሻሻያው ከኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር ጋር በተያያዘም መሰረታዊ የሚባሉ ለውጦችን አካቷል፡፡ ከእነዚህም መካከል፡-

- ታክስ ከፋዮች የኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልባቸውን ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ወይም በሀገር ውስጥ ለማምረት ከታክስ ባለስልጣን ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡
- የታክስ መሠረቱ ተጨማሪ የታክስ ጫና ሳያስከትል (revenue neutral) ከማምረቻ ወጪ ወደ የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ እንዲሆን ተደርጓል፡፡
- በተወሰኑ ከውጭ በሚገቡ እቃዎች ላይ በተለይም ባገለገሉ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር እንዳይገቡ የሚያደርግ ከ100 እስከ 500 በመቶ የሚደርስ የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ እንዲጣል ተደርጓል፡፡
- በፊት ኤክሳይዝ ታክስ የማይከፈልባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ታክሱ እንዲጣልባቸው ተደርጓል፡፡

### 3.1.4. የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ማሻሻያ

ለረጅም ዓመታት የቆዩ በርካታ ችግሮች ለመቅረፍ 2013 ዓ.ም አጠቃላይ የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያ በማድረግ ማሻሻያው ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ማሻሻያው በዋናነት ትኩረት ያደረገው በጉምሩክ ታሪፍ ደንቡ የነበሩ ችግሮች ለመቅረፍ ዕቃዎች በምርት ደረጃቸው መሰረት የታሪፍ መጣኔ እንዲጣልባቸው ማድረግ ሲሆን፤ ይህም የጉምሩክ ታሪፍ መጣኔ መሰረታዊ ግብአቶች ሆነው በሀገር ውስጥ በበቂ መጠንና ጥራት የማይገኙ እና የካፒታል ዕቃዎች ነፃ፣ በከፊል የተመረቱ እና ምርቶችን ለማሸግ የሚያስፈልጉ እንዲሁም መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ከ15 በመቶ የበለጠ እንዳይሆን ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ማሻሻያው ቀደም ሲል የነበረውን የጉምሩክ ታሪፍ ተመን አደረጃጀት ወይም የመጣኔዎች ብዛት ለአስተዳደር በሚያመች መልኩ ከ6 ወደ 5 ዝቅ እንዲል የተደረገ ሲሆን፤ መጣኔዎቹም ከ0 በመቶ፣ 5 በመቶ፣ 10 በመቶ፣ 20 በመቶ፣ 30 በመቶ እና 35 በመቶ ወደ 0 በመቶ፣ 5 በመቶ፣ 15 በመቶ፣ 25 በመቶ እና 35 በመቶ እንዲቀየር ተደርጓል፡፡በተጨማሪም ጥሬ ዕቃዎች፣ የካፒታል ዕቃዎች፣ በከፊል የተመረቱ ግብአቶች እና መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች በዋናነት የሚገኙበት መጣኔያቸው ከ0 በመቶ እስከ 15 በመቶ የሆኑትን የሱር ታክስ እንዳይመለከታቸው ተደርገዋል፡፡ በሌላ በኩል በሀገር ውስጥ ሊተኩ ለሚችሉ በቂ ከለላ በሚሰጥ መልኩ፤ እንዲሁም በአመዛኙ የቅንጦት ዕቃዎች እና ተሽከርካሪዎች ላይ የታሪፍ መጣኔው ከ25 እስከ 35 በመቶ እንዲሆንና የሱር ታክስም እንዲመለከታቸው ሆኖ ስራ ላይ ውሏል፡፡

ከማሻሻያው በፊት የተወሰኑ አምራቾች ግብአት ከውጭ በማስገባት በሀገር ውስጥ እሴት በመጨመር ገቢ ምርቶችን ለመተካት እንዲችሉ ከለላ በመስጠት በሀገር ውስጥ ገበያ በዋጋ

ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ ዓላማ ያደረገ ነበር። ይህም አምራቾች ብቻ የሚስተናገዱበት ራሱን የቻለ በታሪፍ ደንቡ የሁለተኛ ሀ ታሪፍ መደብ የሚባል የነበረ ሲሆን፤ በዚህ አሰራ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው አምራቾች እና ገጣጣሚዎች ዕቃዎቹን ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ሲያስገቡ በዋናዉ የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ለተመሳሳይ ዕቃ ከተቀመጠው የጉምሩክ ታሪፍ መጣኔ በታች የሚስተናገዱበት ነበር። ሆኖም ይህ አሰራር ረጅም ሂደት የሚጠይቅና የተለያዩ ተቋማትን የሚያካትት በመሆኑ ለአምራቾች የማይመች የነበረ ከመሆኑም በላይ ላልተፈለገ ዓላማ ሲውል የነበረና የሚፈለገውን ውጤት ማስገኘት ያልቻለ ነበር። በተለይ የታሪፍ አመዳደቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶችን ሙሉ በሙሉ በማግለል ከፍተኛ የኢንቨስትመንት መጠን ያላቸውን ብቻ የሚጠቅም ነበር። በመሆኑም የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያው እነዚህንና ሌሎች በርካታ ችግሮችን በዘላቂነት ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

### 3.1.5. የሱር ታክስ ማሻሻያ

የሱር ታክስ ስራ ላይ እንዲውል የተደረገው በ1999 ዓ.ም ሲሆን፤ ከነዳጅ ምርቶች፣ የካፒታል ዕቃዎች፣ የጭነት እና የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፣ አውሮፕላኖች እና የአፈር ማዳበሪያ በስተቀር በሁሉም የገቢ ዕቃዎችላይ በመጣል የሚሰበሰብ ነው። ከዚህ የሚሰበሰብ ገቢ መንግስት በወቅቱ ተከስቶ የነበረውን የዋጋ ግሽበት በዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የማህበረሰብ ክፍል ሊደርስ ከሚችል ከፍተኛ ጫና ለመቀነስ እንዲቻል በጊዜያዊነት የተጣለ ቢሆንም፤ ታክሱ አሁንም በሥራ ላይ ይገኛል። ታክሱ ከጠቅላላ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከሚሰበሰበው ገቢ እስከ 20 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ በማበርከት የታክስ ስርዓቱ ቁልፍ አካል ሆኖ ቀጥሏል።

ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ከጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ማሻሻያ ጋር በተያያዘ ጥሬ ዕቃዎች፣ በከፊል የተፈበረኩ ዕቃዎች፣ የካፒታል ዕቃዎች እና መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች የጉምሩክ ታሪፍ መጣኔያቸው ከ0 እስከ 15 በመቶ የሆኑት የሱር ታክስ እንዳይመለከታቸው ተደርገዋል። ይህም የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓቱ እና የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ አከፋፈሉ ቀላል እንዲሆን የሚያግዝ በመሆኑ ኢንቨስትመንትን ያበረታታል ተብሎ ይጠበቃል[2]።

---

[2] ከ15% በላይ የጉምሩክ ቀረጥ ማጠን ያላቸውከውጭየ ሚ ቡ ምርቶች በአጠቃላይ 10% ቀረጥ ይገዛሉ። ነገር ግን በዋነኛነት በልብስ እና ጨርቃጨርቅ ምድብ ውስጥ 25% የጉምሩክ ቀረጥ የሚጣልባቸውነገር ግን ሙሉ በሙሉ ከሱርክስ ክፍያ ነፃ የሆኑ የተወሰኑ ከውጭየ ሚ ቡ ምርቶች አሉ።


### 3.1.6. የታክስ ማበረታቻ አስተዳደሩ በአንድ ማዕከል እንዲሆን መደረጉ

ከዚህ በፊት ከ35 በላይ በሚሆኑ የመንግስት ተቋማት ሲሰጥ የነበረውን የቀረጥና ታክስ ነጻ እና ማበረታቻ በትክክል ለሚገባው መሰጠቱን እና አፈጻጸሙን ለመከታተል በሚያመች መልኩ ለማስተዳደር እንዲቻል በአንድ መስኮት የኢሌክትሮኒክ አገልግሎት በመደገፍ ከግንቦት 2013 ዓ/ም ጀምሮ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል እንዲሆን ተደርጓል። በዚህም የገንዘብ ሚኒስቴር የታክስ ማበረታቻ እና የታክስ ነፃ አሰጣጥ ሂደቱን በማስተባበር እና የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በህጉ መሰረት ትክክል ስለመሆናቸው በማረጋገጥ ውሳኔ የመስጠት ስራ በማከናወን ላይ ይገኛል። ይህን ማሻሻያ ተከትሎ የገንዘብ ሚኒስቴር ከ2014 ዓ/ም ጀምሮ ለታክስ ማበረታቻው እና ለታክስ ነጻ የተሰጠውን የገንዘብ መጠን ሪፖርት የማዘጋጀት ሥራ የጀመረ ሲሆን፤ በአሰራሩ መሻሻል ምክንያት በዚሁ ዓመት ሊታጣ ይችል የነበረውን ከብር 16 ቢሊዮን በላይ ማዳን ተችሏል።

### 3.1.7. የታክስ ማበረታቻ ማሻሻያ

የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን በትክክል ሥራ ላይ ለመዋል እንዲቻል የሚደረገውን ጥረት ለማሳካት የሚያግዝ ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱን የቻለ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር 517/2014 በ2014 ዓ.ም ሥራ ላይ ውሏል። ይህ የማበረታቻ ደንብ የኢንቨስትመንት ስርጭቱን ተደራሽ በማድረግ ከኢንቨስትመንት ሊገኝ የሚችለውን የስራ ዕድል እና ሌሎችንም ጥቅሞች ፍትሃዊ እንዲሆን ከአዲስ አበባ እና ዙሪያው ያላቸውን ርቀት ከግምት ውስጥ በማስገባት በዝርዝር ተደንግጓል። በተጨማሪም ማሻሻያው ኢንቨስትመንት ለመሳብ ሚና የሌላቸው፤ ነገር ግን መንግስትን ከፍተኛ የቀረጥና ታክስ ገቢ የሚያሳጡ የማበረታቻ አይነቶች እንዲነሱ ተደረጓል። ከነዚህም ውስጥ የቀረጥና ታክስ ገቢ በማሳጣት ግንባር ቀደም ሚና የነበረውን የተሽከርካሪ ቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲነሳ ተደርጓል። ከምስል 3.2 መመልከት እንደሚቻለው በኢትዮጵያ በቀረጥና ታክስ ነጻ ሲታጣ የነበረው ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በ2013 ዓ/ም 1.58 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2016 ዓ/ም (የ2016 ዓ/ም ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የዓለም የገንዘብ ድርጅት ትንበያ ነው) ወደ 0.8 በመቶ ዝቅ ማለቱ ነው።

**ምስል 3.2 የታክስ ወጪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በመቶኛ (2013-2016 ዓ/ም)፤**




| | ልዩ ሁኔታ | የግል ዘርፍ ኢንቨስትመንት | የመንግስት ልማት ድርጅቶች | በጎ አድራጎት ድርጅቶች | አካል ጉዳተኞች | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2013 | 1.11 | 0.35 | 0.10 | 0.01 | 0.02 | 1.58 |
| 2014 | 1.05 | 0.19 | 0.08 | 0.01 | 0.01 | 1.43 |
| 2015 | 0.66 | 0.17 | 0.07 | 0.00 | 0.00 | 0.89 |
| 2016 | 0.58 | 0.17 | 0.05 | 0.00 | 0.00 | 0.80 |


*ምንጭ፡ የዓለም የገንዘብ ድርጅት ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት፣ የጉምሩክ ኮሚሽን እና የታክስ ፖሊሲ መምሪያ ስሌቶች*

የዚህ ማሻሻያ አካል የሆነው በሀገር ውስጥ የማይገኝ እውቀት ያላቸው የውጭ ሀገር ባለሙያዎች የሚከፈላቸው ደመወዝ ከታክስ ነጻ እንዲሆን በማድረግ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት እና የእውቀት ሽግግር በማምጣት የሀገር ውስጥ አቅም ለማሳደግ ሲሰጥ የነበረው ማበረታቻን እንዲነሳ ተደርጓል፡፡ ይህ ማበረታቻ እንዲነሳ የተደረገው በተጠበቀው ደረጃ የእውቀት ሽግግር ማምጣት ካለመቻሉም በላይ የመንግስትን ገቢ በማሳጣቱ እና በተመሳሳይ ሥራ የተሰማሩ ወይም የተሻለ እውቀት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በመፍጠሩ ነው፡፡ በህጉ በተደነገገው መሰረት በሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት መደረግ የነበረበት ክትትልና ቁጥጥር ባለመደረጉ በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ሊሰሩ የሚችሉ ስራዎች ከውጭ በሚመጡ ዜጎች እንዲሰሩ፣ ከፍተኛ ደመወዝ በመክፈል የትርፍ ገቢ መሰረትን በማጥበብ የታክስ ገቢ ማሳጣቱ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ያለአግባብ ወደ ውጭ እንዲወጣ በማድረጉ ነው፡፡ ስለሆነም ይህንን ያልተፈለገ ውጤት ከግምት ውስጥ በማስገባት ማበረታቻው እንዲሻር ተደርጓል፡፡

### 3.1.8. የማህበራዊ ልማት ቀረጥ

ከጉምሩክ ቀረጥ ማሻሻያ ጋር በተያያዘ የሱር ታክስ እንዲነሳላቸው በተደረጉ ዕቃዎች ምክንያት ሊታጣ የሚችለውን ገቢ ለመተካት እና የፌዴራል መንግስት ቀጣይነት ያለው የገቢ ምንጭ እንዲሆን ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ሁሉም ምርቶች ላይ የ3 በመቶ መጣኔ ያለው የማህበራዊ ልማት ቀረጥ በደንብ ቁጥር 519/2014 እንዲጣል ተደርጓል፡፡

**ምስል 3.3. የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያ ያስገኙት ገቢ ማጠቃለያ (በቢሊዮን ብር)**




*ምንጭ ፡ በገንዘብ ሚኒስቴር የታክስ ፖሊሲ መምሪያ የጥናት ሪፖርቶች*

## 3.2. በቅርብ ጊዜ በታክስ አስተዳደር የተከናወኑ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች

የኢትዮጵያ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ራስን የመመዘን ስርዓት ከታክስ ማስከበር ጋር ተደምሮ የሚተገበር ነው፡፡ በመሆኑም ታክስ ከፋዮች ወቅቱን ጠብቀው ታክሳቸውን በማሳወቅ በታክስ ህጉ በተደነገገው መሰረት ለታክስ አስተዳደሩ የሚገባውን ታክስ በወቅቱ እንዲከፍሉ ይገደዳሉ፡፡

ኢትዮጵያ የፌዴራል አወቃቀር የምትከተል ሲሆን፤ የታክስ እና የወጪ መዋቅሩ በዚሁ አግባብ ባልተማከለ የመንግስት አደረጃጀት የሚከናወን ነው፡፡ ይህ ያልተማከለ አስተዳደር በመርህ ደረጃ የመንግስት አገልግሎቶች ወደ ክልሎች ብሎም ወደ ህዝቡ እንዲደረስ ከማድረግ አንጻር ተመራጭ ሲሆን፤ እንደ ወጪ ሁሉ የታክስ አስተዳደር ስርዓቱም በፌዴራል፣ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የሚከናወን ነው፡፡

በ2010 ዓ.ም በፌዴራል የመንግስት ተቋማት በተደረገ የአደረጃጀት ለውጥ መሰረት የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሰረት የገቢዎች ሚኒስቴር

የተባለ ሲሆን፤ የጉምሩክ ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለገቢዎች ሚኒስቴርሆኖ ሚኒስቴሩ ኮሚሽኑን የመከታተል እና የመቆጣጠር ሥልጣን ተሰጥቶታል።

### 3.2.1. የተከናወኑ ዋና የታክስ እና የጉምሩክ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች

የገቢዎች ሚኒስቴር የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል፣ የታክስ ተገዢነትን ለማሳደግ፣ የታክስ ህግን ለማስከበር እና የገቢ አሰባሰብን በዘላቂነት ለማሳደግ በታክስ አስተዳደር ስርዓቱ ላይ ሁሉን አቀፍ ለውጥ በማድረግ ላይ ይገኛል። የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በታክስ አስተዳደር ስርዓቱ ላይ የሚከተሉትን ዋና ዋና ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ተግባራዊ አድርጓል።

**ሀ) የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች**

- የታክስ አስተዳደር ሂደቶችን ለማቀላጠፍ እና ተገዢነትን ለማበረታታት የሚያግዙ የተለያዩ መመሪያዎችን ማውጣት እና መተግበር፣ ቅጣቶችን ማስወገድ፣ ግምታዊ ግምገማዎች እና የታክስ ክፍያ ማራዘሚያ ስራዎች ተከናውነዋል።
- የራስን መገምገም ማሻሻያ፤ የንግድ ሥራ ከተቋረጠ በኋላ የገቢ ግብር መክፈል እና የታክስ ክሊራንስ አገልግሎቶችን የመሳሰሉ እርምጃዎች ስራ ላይ ውለዋል።
- የታክስ ማጭበርበርን ለመቀነስ በስጋት ላይ የተመሰረተ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ አሰራር እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ስርዓቶችን ከባዮሜትሪክ ማረጋገጫ ጋር ተተግብረዋል።
- አሰራሮችን በማዘመን እና ዲጂታል በማድረግ የገቢ አሰባሰብን ለማሻሻል የኢ-ፋይል፣ የኢ-ክፍያ ሥርዓቶች እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተግባራዊ ተደርገዋል።
- በስጋት ላይ የተመሰረተ ኦዲት፣ የግብር ከፋይ ትምህርት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት የታክስ ተገዢነትን የማሻሻል ተግባራት ተከናውነዋል።
- የታክስ አሰባሰቡን ለማሻሻል የሚያስችሉ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት፣ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኞችን ማስተዋወቅ እና የመረጃ ቋት በመተግበር የማዘመን ስራዎች ተሰርተዋል።
- የታክስ የህግ ተገዥነት ለማሳደግ ለግብር ከፋዮች እና ሰራተኞች የሽልማት መርሃ ግብሮችን ስራ ላይ ውሏል።

ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው የታክስ አስተዳደር ስርዓት ለማዘመን በርካታ መሻሻሎች የታዩ ቢሆንም አሁንም ቀጣይ የሪፎርም እና የማሻሻያ ስራዎች በመተግበር የታክስ

አስተዳደር ስርዓቱን ማሻሻል እና ማዘመን ያስፈልጋል። የታክስ አስተዳደር ውጤታማ የሚባለው አብዛኛዎቹን ታክስ ከፋዮች በበቂ ሁኔታ በማሳመን በራስ ፍላጎት ታክስ የመክፈል ግዴታቸውን እንዲወጡ በማድረግ በአንጻሩ በህግ ማስከበር ታክስ የሚከፍሉ ታክስ ከፋዮች ዝቅተኛ ማድረግ የሚችል ሲሆን ነው። የታክስ አስተዳደሩ የታክስ ተገዥነትን የሚያበረታቱ አገልግሎትን ትኩረት ያደረጉ ተግባራት ማለትም የማስተማር፣ የማገዝ፣ ወዘተ ጥረቶች በማድረግ እና ታክስ በሚሰውሩ እና በማጭበርበሩ ላይ ጠንካራ የህግ እርምጃ በመውሰድ የታክስ ተገዥነትን ማጠናከር እና መሰረታዊ የታክስ መርሆችን መሰረት በማድረግ የታክስ አስታደደር ስራውን ማከናወን አለበት (Okello, 2014)።


ከዚህ አንጻር የአንድ የታክስ አስተዳደር ጤናማነት ምዘና (TADAT) ውጤት አሰጣጥ መሰረት ከፍተኛው ኤ(A) ዝቅተኛው ዲ(D) ደረጃ የሚያሰጥ ሲሆን፤ እ.ኤ.አ በ2016 በተደረገው ምዘና የሀገራችን የታክስ አስተዳደር በአማካይ ዝቅተኛውን ዲ(D) ደረጃ አግኝቷል። የምዘናው ውጤት ደረጃ ታክስ ከመሰብሰብ አፈጻጸም ጋር ሊኖረው የሚችል ተያያዥነት ለማጥናት በተደረገ ጥናት ከሰሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ ሀገራት ዝቅተኛ የምዘና ደረጃ ያገኙ ሀገራት ዝቅተኛ የገቢ አፈጻጸም እንደነበራቸው ተረጋግጧል። በዚህም መሰረት የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻአፈፃፀም ከሀገራቱ የምዘና ውጤት ደረጃ ጋር በንፅፅር ሲታይ ዲ(D) የሆኑ ዝቅተኛ 4.7 መካከለኛ 11.4፣ ሲ(C) ዝቅተኛ 10 መካከለኛ 13.7፣ ቢ(B) ዝቅተኛ 10.8 መካከለኛ 18.6 እና ኤ(A) ዝቅተኛና መካከለኛ 18.3 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም የኢትዮጵያ የምዘና ውጤት አማካይ ደረጃ ዲ(D) ሆኖ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻው በ4.7 እና በ11.4 በመቶ መካከል የሚገኝ ወይም 6.8 በመቶ መሆኑ የሚገርም አይሆንም። በመሆኑም የሀገራችን የምዘና ውጤት ደረጃ በአማካይ ከዲ(D) ወደ ሲ(C) ማሻሻል የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ ከ3.2 እስከ 6.9 በመቶኛ ከፍ ሊያደርገው እንደሚችል ይገመታል (Acedo *et al* , እ.ኤ አ 2022)።

ሰንጠረዥ 3.1፡ የታክስ አስተዳደር ጤናማነት ምዘና (TADAT) የደረጃ ውጤት መግለጫ፤

| ደረጃ | የደረጃ ውጤት መግለጫ | የደረጃ ውጤት |
|---|---|---|
| ኤ (A) | የዓለም አቀፍ እና በላይ መስፈርት የሚያሟላ ጥሩ የታክስ አስተዳደሩ | 4.00 |
| ቢ (B) | ከጥሩ በታች ነገር ግን ደህና የሚባል የታክስ አስተዳደር መስፈርት ያለው | 3.00 - < 4.00 |
| ሲ (C) | መሰረታዊ የሚባሉ የታክስ አስተዳደር መስፈርቶች ያሉበት | 2.00 - < 3.00 |
| ዲ (D) | መሰረታዊ የሚባሉ የታክስ አስተዳደር መስፈርቶች የሌሉበት | 1.00 - < 2.00 |

ምንጭ፡- በTADAT ሴክሬታሪያት እ.ኤ.አ ታህሳስ 10 ቀን 2021 በግሎባል ታክስ ፕሮግራም የቀረበ፤

## የTADAT ውጤቶች እና የግብር-ወደ-GDP ጥምርታ ለኤስኤስኤ አገሮች[3]




*ማስታወሻ- ግራፉ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ጥምርታ በTADAT ደረጃ ያሳያል። በግልጽ እንደሚታየው በአማካይ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ጥምርታ ዝቅተኛ የTADAT ደረጃ ያላቸው አገሮች ማለትም D ዝቅተኛ ሲሆኑ፣ ከፍተኛ የTADAT ደረጃ ያላቸው ከፍተኛ ነው።*

*ምንጭ-* Acedo *et al* (2022)


ከዚህ በተጨማሪ የሀገራት የታክስ ገቢ አሰባሰብን በታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ እና ከንግድ ስራ ትርፍ የሚገኝ ገቢን ከጠቅላላ የታክስ ገቢ ያለው ድርሻ መሰረት በማድረግ ማነጻጸር እንደሚቻል ያመለክታል። በዚህም የንግድ ስራ ትርፍ ገቢ ከጠቅላላ የታክስ ገቢ ያለው ድርሻ ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝ የታክስ ገቢ አፈጻጸሙ ከፍተኛ ስለመሆኑ ወይም የሚሰበሰበው የታክስ ገቢ ኢኮኖሚው ማመንጨት የሚችለውን ዕምቅ ዓቅም አሟጦ መሰብሰቡን የሚያመላክት ይሆናል። በዚህ መስፈርት አንጻርም ሲታይ የሀገራችን አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆኑን ወይም ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች ላይ የተመሰረተ

[3]የTADAT ማዕቀፍ የታክስ አስተዳደር አፈጻጸምን የሚገመግመው የአፈጻጸም ውጤት አካባቢዎች (POAs) በመባል በሚታወቁ ዘጠኝ ወሳኝ አካባቢዎች የታክስ አስተዳደር አፈጻጸምን ይገመግማል: የተመዘገበው የታክስ ከፋይ መሠረት ታማኝነት፣ ውጤታማ የአደጋ አስተዳደር፣ የበጎ ፈቃደኝነት ተገዢነትን መደገፍ፣ የታክስ መግለጫዎችን በወቅቱ ማቅረብ፣ የታክስ ክፍያ በወቅቱ መክፈል፣ በአዋጅ ትክክለኛ ሪፖርት ማድረግ ውጤታማ የታክስ አለመግባባት አፈታት፣ ውጤታማ የገቢ አስተዳደር እና ተጠያቂነትና ግልጽነት።
የ TADAT ውጤቶች እንደሚከተለው ተከፋፍለዋል:

መ: ጠንካራ አፈፃፀም (ከአለምአቀፍ ጥሩ ልምምድ ጋር ያሟላል ወይም ይበልጣል)
ለ: ጥሩ አፈጻጸም (ጤናማ የአፈጻጸም ደረጃ ግን ከዓለም አቀፍ ጥሩ ልምምድ በታች)
ሐ: ደካማ አፈጻጸም (ከዓለም አቀፍ ጥሩ ልምምድ ጋር በተያያዘ)
መ: በቂ ያልሆነ አፈጻጸም (ለ C ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ መስፈርቶች አልተሟሉም)

ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል:: ስለዚህ የታክስ አስተዳደሩን የምዘና ውጤት ደረጃ የሚያሻሽሉ የሪፎርም እና የማሻሻያ ስራዎች በማከናወን የታክስ ገቢን ማሳደግ ይቻላል::

ምስል 3.3. የተመረጡ አገሮች የ2018 የግብር አስተዳደር አመላካቾች ሁኔታ




ምንጭ:- በአፍሪካ፣ UNECA (2019) ቀጣይነት ያለው ልማትን የፋይናንስ ለማድረግ የፊስካል ፖሊሲ

### ለ) ዋና የጉምሩክ አስተዳደር ማሻሻያዎች

- የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓቱን ከASYCUDA ወደ ኤሌክትሮኒክ የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት (eCMS) አሻሽሏል::
- የጉምሩክ ዋጋ አሰጣጥ ስርዓትን የማዘመን ስራ ተሰርቷል::
- ለወጪ እና ገቢ ንግድ የሚጠየቁ ሰነዶች ቀላል እንዲሆኑ ተደርጓል::
- የጭነት መፈተሻ ማሽኖች እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመከታተያ ስርዓቶች እና የተፈቀደ የኢኮኖሚ ኦፕሬተሮች ፕሮግራም ተተግብሯል።
- በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ፈጣን የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት ስራ ላይ ውሏል::

# 4. ብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች

ብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂው የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ በማሳደግ እና የመንግስት 10 ዓመት የልማት እቅድ ለማሳካት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ ለመሰብሰብ እንዲያስችል የተቀረጸ ነው፡፡ በመሆኑም የስትራቴጂው አጠቃላይ ዓላማ የሀገር ውስጥ የገቢ ዕምቅ ዓቅም ሙሉ በሙሉ አሟጦ በመሰብሰብ የመንግስት የልማት ፖሊሲ ነጻነት በማስጠበቅ የሀገራችን የብልጽግና ጉዞ እውን ለማድረግ ሲሆን፤ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡


1. **ዝቅተኛ እና እየቀነሰ የመጣውን የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻን ማሻሻል፡-** ዝቅተኛ እና ከዓመት ዓመት እያሽቆለቆለ የመጣውን የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በስትራቴጂው የተካተቱ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞችን እና ማሻሻያዎችን በመተግበር በስትራቴጂው መጨረሻ የትግበራ ዘመን 13.2 በመቶ ማድረስ፤
2. **የታክስ መሰረቱን ማስፋት፡-** አዳዲስ የታክስ ዓይነቶች እንደ ንብረትና የተሽከርካሪ ዝውውር ታክስ ሥራ ላይ በማዋል፤ እንዲሁም ስራ ላይ የሚገኙ የታክስ ዓይነቶች በአግባቡ የሚገባቸውን ታክስ የማይከፍሉ ወደ ታክስ መረቡ እንዲገቡ በማድረግ የታክስ ገቢ ማሳደግ እና ፍትሀዊ የገበያ ውድድር በመፍጠር የገቢ ዕድገቱን ዘላቂነት ማረጋገጥ፤
3. **የታክስ ተገዢነትን ማሻሻል፡-** የታክስ አስተዳደሩን በማዘመን እና የታክስ መሰረታዊ መርሆች በትክክል በመተግበር የታክስ ከፋዮችን እምነት በመጨመር፣ የታክስ ሰብሳቢ ባለሙያዎችን ዓቅም እና ስነ-ምግባር በማሻሻል እና አጠቃላይ ህብረተሰቡ ለታክስ ማጭበርበር እና ስወራ የማይመች በማድረግ በራስ ተገዥነት ታክስ የመክፈል ባህልን ማሳደግ፤
4. **ኢ-መደበኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ወደ ታክስ መረቡ ማስገባት፡-** መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍ ወደ ታክስ መረቡ በማስገባት የታክስ መሰረቱን ማስፋት፤
5. **የታክስ ስርዓቱ የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ፡-** ሀገራችን የፌዴራል ስርዓት የምትከተል ሀገር በመሆኗ በታክስ ፖሊሲ እና በታክስ አስተዳደር በፌዴራል፣ በብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት እና በከተማ አስተዳደር ደረጃ የሚገኙትን ገቢ

ሰብሳቢ ተቋማት በአደረጃጀትም ሆነ በቴክኖሎጂ ወደ ተመሳሳይ ደረጃ እንዲዘምኑ ማድረግ፤

እነዚህ ዓላማዎች የታክስ ፖሊሲን በማጠናከር እና የታክስ አስተዳደር አቅምን በማሳደግ ተግባራዊ ይደረጋሉ። ይህ ሁሉን አቀፍ ሪፎርም እና ማሻሻያ የኢንቬስትመንት ምቹነትን ለማሻሻል፣ የግሉ ዘርፍ ልማትን ለማነቃቃት እና በታክስ ሥርዓቱ ውስጥ የላቀ ግልጽነትን እና ፍትሃዊነትን ለመፍጠር የሚያግዝ እንዲሆን ይሆናል።

በስትራቴጂው የተመለከቱ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች በመተግበር በስትራቴጂው የመጨረሻ የትግበራ ጊዜ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ በ6.9 በመቶኛ በመጨምር 13.2 በመቶ እንዲደርስ የሚሰራ ይሆናል። ይህም ተጨማሪ ገቢ 4 በመቶኛ ከታክስ ፖሊሲ እና ቀሪው 2.9 መቶኛ ከታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች የሚገኝ ነው።

ምስል 4.1. የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በመቶኛ ትንበያ (2017-2020 በጀት ዓመት)




*ማሳሰቢያ* ፡ ሰማያዊዎቹ ግራፎች በአፈጻጸም የነበረውን፤ በአረንጓዴ ግራፍ የተመለከቱት በስትራቴጂው ጊዜ ይደርሳል ተብሎ የተያዘ ትንበያን የሚያሳዩ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በመቶኛ ናቸው። የ2016 በጀት ዓመት አሃዝ የአለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ትንበያን መሰረት ያደረገ ነው።

*ምንጭ* ፡ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የታክስ ፖሊሲ መምሪያ ትንበያ

ማጥን: የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ ተግባራዊ ሲደረግ ትኩረት የሚሰጣቸው መርሆዎች

**ገለልተኝነት፡-** የታክስ ስርዓቱ ተመሳሳይ የኢኮሚኖ እንቅስቃሴዎችን በተመሳሳይ መንገድ ማስተናገድ ይኖርበታል፡፡ ይህ የታክስ መርህ የኢኮኖሚ ተወናዮች ውሳኔ በሚወሰንበት ጊዜ የታክስ ስርዓቱ በውሳኔ ላይ ሚና እንዳይኖሮው ያደርጋል (የኢኮኖሚ ማዛባትን ያስቀራል)፡፡

**ለመረዳት እና ለመተግበር ቀላል፡-** የታክስ ስርዓቱ ታክስ ከፋዩ፣ ታክስ ሰብሳቢ ባለስልጣኑ እና ህብረተሰቡ በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉት አግባብ መቀረጽ አለበት፡፡ በተጨማሪም የታክስ ስርዓቱ የታክስ ሰብሳቢው ባለሥልጣን ታክሱ ለመሰብሰብ የሚያወጣው ወጪ ዝቅተኛ የሆነ እና ታክስ ከፋዩ ታክስ ለመክፈል ወይም ታክስ የመክፈል የተገዥነት ግዴታውን ለመወጣት ብዙ ወጪ የማያስወጣ መሆን አለበት፡፡ ይህ መርህ የማያሟላ የታክስ ስርዓት ሌሎች መሰረታዊ የጥሩ የታክስ ስርዓት መገለጫዎች የሆኑ መርሆች እንዲሸረሸሩ በማድረግ የታክስ ተገዥነትን በመቀነስ ለታክስ ስወራ ይዳርጋል፡፡

**ከጊዜ እና ከሁኔታዎች የሚጣጣም፡-** በተለይ በሀገራችን እንደልማድ የሆነውና መቀየር ያለበት አንድ የታክስ ህግ ከነችግሩም ቢሆን ሳይሻሻል ለረጅም ዓመታት መቆየት እንደ ጥሩ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህ ስህተት እና መቀየር ያለበት ልማድ ሲሆን፤ አንድ የታክስ ፖሊሲ እና ህግ ስራ ላይ ሲውል ነባራዊ ሄኔታዎች እና በቀጣይ ሊፈጠሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በጥንቃቄ ስራ ላይ መዋል ያለበት ቢሆንም አስፈላጊውን ጥናት በማድረግ እንደየሁኔታው ማሻሻያዎች ማድረግ የአንድ የታክስ ስርዓት ጥሩነት መገለጫ ነው፡፡

**ተፈጻሚነት፡-** የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ ህግ በሚቀረጽበት ጊዜ የታክስ አስተዳደሩ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡ ምንም ያክል ጥሩ ፖሊሲ እና ህግ ቢቀረጽም የታክስ አስተዳደሩ የመፈጸም አቅም እና ሁኔታ ከግምት ውሰጥ ያላስገባ በሚሆንበት ጊዜ የሚጠበቀውን ውጤት ማግኘት አይቻልም፡፡


**ፍትሀዊነት፡-** በተመሳሳይ የገቢ ደረጃ የሚገኙ ታክስ ከፋዮች ተመሳሳይ የታክስ መጠን መክፈል አለባቸው፡፡ ይህን የማያሟላ የታክስ ስርትዓት ኢፍትሃዊ ስለሚሆን ታክስ ከፋዮች በመንግስት ላይ የሚኖራቸው እምነት ዝቅተኛ ስለሚሆን የታክስ መክፈል ፍቃደኝነታቸው እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

## 4.1. የብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ ስልት

የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ የሀገሪቱን ዕምቅ የገቢ አቅም ሙሉ በሙሉ ለመሰብሰብ እንዲቻል በ2004 በጀት ዓመት የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ ፕላን እና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትሮችን እንዲሁም የብሔራዊ ባንክ ገዥን ያካተተ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ተቋቁሟል፡፡ ይህ ኮሚቴ ሲሰራው የነበረን ስራ በይበልጥ በተሻለ ደረጃ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ

አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ተግባራዊ ለማድርግ እንዲቻል መንግስት የጠቅላይ ሚኒስቴር ሲኒየር የማክሮ ኢኮኖሚ አማካሪ በሆኑ የሚመራ ብሔራዊ የታክስ ሪፎርም ታስክ ፎርስ በሐምሌ ወር በ2016 ዓ/ም እንደገና ተቋቁሟል፡፡ የታስክ ፎርሱ ስራውን የሚያግዝ ብሔራዊ የታክስ ሪፎርም ቴክኒክ ኮሚቴ በማቋቋም እና ይህን በየተቋማቱ በየደረጃው ሪፎርሙን የሚከታተሉ የታክስ ሪፎርም ዩኒቶች እንዲደራጁ አድርጓል፡፡

ምስል 4.2. የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ የአስተዳደር ግንኙነቶ




*ምንጭ ፡ ከአለም ዓቀፉ የገንዘብ ድርጅት የተወሰደ*

ብዙ ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች (Low and Middle income Countries) በጣም ጥሩ የታክስ ፖሊሲ እና ህግ በመቅረጽ ውጤት ለማግኘት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ሆኖም የታክስ ፖሊሲዎቹ እና ህጎቹ የታክስ አስተዳደሩን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወኑ ስለማይሆኑ ወይም ማከናወን ስላለባቸው የታክስ አስተዳደር ማሻሻያዎች አብሮ

ታቅደው ስለማይከናወኑ ውጤታማ ሳይሆኑ ይቀራሉ (Vehorn, 1997)፡፡ ስለሆነም በታክስ ፖሊሲ አውጪው እና በታክስ አስተዳደር ተቋሙ መካከል ያሉትን የማይነጣጠሉ ኃላፊነቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት በቅንጅት መስራት ጥሩ የታክስ ስርዓት በመፍጠር የሚፈለገውን ገቢ ለመሰብሰብ፣ አመቺ የቢዝነስ እና የኢንቨስትመንት ከባቢ በመፍጠር የገቢ ዘላቂነትን ማረጋገጥ እና ሌሎች ሀገራዊ ፖሊሲዎች ውጤታማ ለማድረግ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በዚህ መልኩ በቅንጅት በመስራት የታክስ አስተዳደር ስርዓቱን ውጤታማ በማድረግ መንግስት የሚያቅዳቸው ሌሎች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ስራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ያግዛል፡፡ በታክስ ፖሊሲ አቀራረፅ፣ በታክስ ህግ አወጣጥ እና በታክስ አስተዳደር ትግበራ ሂደት ውስጥ በሦስቱ ቁልፍ አካላት መካከል ያለውን መስተጋብር ከላይ በምስል 4.2 ተመላክቷል።

## 4.2. የታክስ የፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያ

ባለፉት ስድስት ዓመታት የታክስ ሥርዓቱን ለማሻሻል የሚያስችሉ በርካታ የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች (ለምሳሌ የታክስ ማበረታቻ፣ የፍራንኮ ቫሉታ ቀረጥና ታክስ፣ ኤክሳይዝ ታክስ፣ የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ እና ህጎች፣ ሱር ታክስ ማሻሻያ) ተደርገዋል፡፡

ሆኖም በተደረገው ጥረት የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ መሻሻል ካለማሳየቱ በተጨማሪ ከዓመት ዓመት የመቀነስ ሂደቱን ለማስቆም አልተቻለም፡፡ ይህም እስከ አሁን ከተደረጉት የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች በተጨማሪ ቀጣይ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች እንደሚያስፈልጉ ይጠቁማል፡፡ ስለሆነም በሚቀጥሉት አራት ዓመታት ማለትም ከ2017 እስከ 2020 በጀት ዓመት የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ ይህ የፖሊሲ ሪፎርም እና ማሻሻያ በስትራቴጂው የመጨረሻ የትግበራ ጊዜ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ጥምርታ በ4 መቶኛ[4] የማሳደግ ዓላማ ይኖረዋል፡፡ ይህም በስትራተጂው የትግበራ ዘመን መጨረሻ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ ለማሻሻል የሚደረገውን ጥረት ለማሳካት ያግዛል፡፡

[4] ከታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች የሚገኘው 3 በመቶውን ሲሆን ቀሪው 1 በመቶውን ከውጭ ምንዛሪ ሪፎርም እና የኢኮኖሚ መንሰራራት የሚገኝ ይሆናል።

### 4.2.1. የገቢ ግብር ሪፎርም እና ማሻሻያ

በ2008 ዓ.ም በተደረገው የገቢ ግብር ህጎች ማሻሻያ በርካታ ለውጦች ተደርገዋል፤ ከነዚህም ውስጥ ቁርጥ ግብር የሚከፈልበት ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ከብር 100,000.00 ወደ ብር 500,000.00 ከፍ እንዲል መደረጉ፣ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር አወቃቀር እና ከገቢ ግብር ነጻ የሆነ ገቢ ከፍ እንዲል መደረጉ ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሆኖም ከሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ጋር በተጣጣመ መልኩ ተጨማሪ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የሚከተሉት ዋና ዋና ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች በስትራቴጂው ዘመን ውስጥ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

- **በስራ ላይ ያለውን የገቢ ሰንጠረዥ ስርዓት ማሻሻል፦** አሁን ባለው የገቢ ሰንጠረዥ የተለያዩ የገቢ ምንጮችን በተናጠል የገቢ ግብር እንዲከፈል የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም ከመቀጠር የሚገኝ የገቢ ግብር ሰንጠረዥ ሀ፣ ከቤት ኪራይ የሚገኝ የገቢ ግብር ሰንጠረዥ ለ፣ ከንግድ ስራ የሚገኝ የገቢ ግብር ሰንጠረዥ ሐ እና ከሌሎች የገቢ ምንጮች የሚገኝ የገቢ ግብር ሰንጠረዥ መ በሚል የተከፋፈለ ሲሆን፤ አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ በላይ የገቢ ምንጭ የሚያገኝ ከሆነ ታክሱን በተናጠል የሚከፍል ሆኖ በየሰንጠረዡ ሊገኝ የሚችል የታክስ ነጻ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ይህ አሰራር መንግስትን የታክስ ገቢ የሚያሳጣ ከመሆኑም በላይ በታክስ ከፋዮች መካከል ፍትሐዊ የታክስ አከፋፈል እንዳይኖር በማድረግ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዳይኖር ያደርጋል፡፡እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ሁሉም የገቢ ምንጮች በአንድ ላይ ታክስ እንዲከፈልባቸው የሚያስችል ስርዓት መተግበር ያስፈልጋል።
- **የታክስ ማበረታቻን ማሻሻል፦** የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣ ኤክስፖርትን ለማሳደግ፣ የስራ ዕድል ለመፍጠር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማምጣት እና ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት የተለያዩ ታክስ ማበረታቻዎች ይሰጣሉ፡፡ ሆኖም አሁን በስራ ላይ ያለው የታክስ ማበረታቻ ከታለመለት ዓላማ አንጻር እያስገኘ ያለውን ጠቀሜታ በመፈተሽ ውጤታማ ያልሆኑና መንግስትን ያለአግባብ ገቢ የሚያሳጡ የማበረታቻ አይነቶችን ማስቀረት ያስፈልጋል። ይህም በተለይ በኢኮኖሚ የበለጸጉ ሀገራት ዝቅተኛ የታክስ መጣኔ ለመጣል በተስማሙበት መሰረት በሀገራችን ከታክስ ነጻ ቢደረግም ከከዚህ በፊቱ በተለየ ታክስ መሰብሰባቸው የሚቀጥሉ በመሆናቸው፤ ይህን ያገናዘበ ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- **የቁርጥ ገቢ ግብር ስርዓትን ቀላል ማድረግ**፡- ዓመታዊ ሽያጫቸው ከ500 ሽህ ብር በታች የሆኑ ታክስ ከፋዮች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው በሽያጭ ግምት ላይ የተመሰረተ የቁርጥ ገቢ ግብር ነው። ይህ የቁርጥ የገቢ ግብር ዘርፈ ብዙ ችግሮች ያሉበት አነስተኛ ታክስ ከፋዮች ወደ ትልቅ ደረጃ እንዳይደርሱ ማነቆ ሆኗል፡፡ ስርዓቱ ውስብስብ፣ ወጥነት የሌለው፣ ለገማቾች መረጃን መሰረት ያላደረገ ግመታ የተጋለጠ፣ ረጅም ዓመታት ያስቆጠረ፣ አሁን ያሉትን ዘርፎች ግምት ውስጥ ያላስገባ ወዘተ በመሆኑ ማሻሻሉ የግድ ይላል፡፡
- **ዝቅተኛ የገቢ ግብር አማራጭ** (MAT)፡- አማራጭ ዝቅተኛ የገቢ ግብር የመንግስትን ገቢ ለማሳደግ የሚያግዝ ከመሆኑ በተጨማሪ የታክስ ስወራ እና ማጭበርበርን በማስቀረት በታክስ ከፋዮች መካከል ፍትሐዊ ውድድር እንዲኖር ያግዛል።
- **የተደራራቢ ታክስ ማስቀረት ስምምነቶችን በመፈተሽ ማሻሻያ ማድረግ**፡- በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከተለያዩ ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ የተደራራቢ ታክስ ማስቀረት ስምምነቶች በመፈረም ስራ ላይ እንዲውሉ አድርጋለች። ስለዚህ በሚቀጥሉት አራት ዓመታት ውስጥ እነዚህ ስምምነቶች ለአገራችን እያስገኙ ያሉትን ጥቅም በሚመለከት በማጥናት ክፍተት ያለባቸውን ስምምነቶች በመለየት የእንደገና ድርድር እንዲደረግ ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አዲስ የሚደረጉ ድርድሮች በተዘጋጀው ብሔራዊ የተደራራቢ ታክስ ማስቀረት ስምምነት የፖሊሲ ማዕቀፍ እና በተሻሻለው የድርድር ሞዴል ብቻ እንዲሆን ይደረጋል፤ እንዲሁም ድርድሮች በተደራጀ አግባብለማከናወን እንዲቻል ከታክስ ፖሊሲ መምሪያ እና ከህግ አገልጎሎት መምሪያ በተውጣጡ የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች የተደራራቢ ታክስ ማስቀረት ኮሚቴ በገንዘብ ሚኒስቴር በማቋቋም የድርድር አቅምን ለማጠናከር የአቅም ግንባት ስራዎች ይሰራሉ።
- **ከመቀጠር የሚገኝ የገቢ ግብርን ማሻሻል**፡- ከመቀጠር የሚገኝ የገቢ ግብር በተለይም ከገቢ ግብር ነጻ የሆነውን ዝቅተኛ የገቢ መጠን አሁን ካለው የኑሮ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ማሻሻያ ይደረጋል።
- **በገቢ ግብር ህጉ በሰንጠረዝ መ ሌሎች ገቢዎች ላይ የሚጣሉ የገቢ ግብር መጣኔዎችን ማሻሻል**፡- በዚህ ሰንጠረዥ የሚገኙ የገቢ ግብር መጣኔዎች ከሌሎች ከሀገራችን ተመሳሳይ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ሀገራትም ይሁን በሀገራችን መሆን ከሚገባቸው የተወሰኑት የታክስ ዓይነቶች ዝቅተኛ መጣኔ ያላቸው በመሆኑ ከሌሎች ማሻሻያዎች በሚጣጣም መልኩ ማሻሻያ ይደረጋል።

### 4.2.2. የንብረት ታክስ

የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት እና የከተማ አስተዳደሮች ለህብረተሰቡ የተሻለ አገልግሎት ማቅረብ እንዲችሉ የገቢ አቅማቸውን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይ ከከተማ መስፋፋት ጋር ተያይዞ እያደገ የመጣውን የመሰረተ ልማት ጥያቄ በበመለስ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ለማረጋገጥ እንዲቻል የክልል እና የከተማ አስተዳደር ገቢን ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ በተጣጣመ መልኩ በሀገር ደረጃ ሥራ ላይ የሚውል የማይንቀሳቀስ ንብረት ታክስ ተግባራዊ ይደረጋል።

### 4.2.3. የሞተር ተሽከርካሪ ዝውውር ታክስ

በአሁኑ ወቅት መንግስት በተሽከርካሪ ባለቤትነት እና ግዥ ላይ የተለያዩ ክፍያዎች በመጣል ገቢ ይሰበስባል፡፡ ነገር ግን አሁን ያሉት ክፍያዎች የሚፈለገውን ገቢ እያስገኙ ካለመሆናቸው በተጨማሪ በተለይ በነዳጅ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች ከፍተኛ የአከባቢ ብክለት የሚያስከትሉ በመሆናቸው የክፍያዎቹ መጣኔ ማሻሻል አሰፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በተጨማሪም መንግስት ከሚሰበስበው ታክስ ክፍተኛ ወጪ በማውጣት መንገድን ጨምሮ የመሰረተልማት ስራዎች የሚሰራ ሲሆን፤ እነዚህን የመሰረተ ልማቶች ለመጠገንም በየዓመቱ ከፍተኛ ወጪ ያወጣል። በእነዚህ የመሰረተ ልማቶች ተጠቃሚ የሚሆኑት መካከለኛ እና ከፍተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገለገሉበት ቢሆንም፤ በስራ ላይ ያለው የክፍያ መጣኔ ይህን የሀብት ክፍፍል ፍትሃዊነት የሚያረጋግጥ አይደልም፡፡ ስለሆነም እነዚህንና ሌሎች ምክንያቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት በስራ ላይ የሚገኙ የክፍያ መጣኔዎችን በማሻሻል የተሽከርካሪ ዝውውር ታክስ የሚጣል ይሆናል፡፡

### 4.2.4. የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ሪፎርም እና ማሻሻያዎች

የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ በፍጆታ ላይ የሚጣሉ ታክሶች ሲሆኑ፤ የሁለቱም ታክሶች ልዩነት ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ነው። ይህ ማለት አሁን በስራ ላይ ባሉ ህጎች መሰረት ዓመታዊ የሽያጭ መጠናቸው ከብር 1 ሚሊዮን በታች የሆኑ የንግድ ስራዎች የተርን ኦቨር ታክስ እንዲሁም ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ዓመታዊ ሽያጭ ያላቸው የንግድ ስራዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲሰበስቡ ተደንግጓል። የተርንኦቨር ታክስዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የንግድ ስራዎች ሽያጭን መሰረት ያደረገ ስለሆነ የታክስ ተገዥነት ወጪን የሚቀንስ እና ለመተግበር ቀላል እንዲሆን ለማድረግ ሲሆን፤ በሌላ

በኩል ተጨማሪ እሴት ታክስ ከሚከፍሉ የንግድ ስራዎች በገበያ ላይ ፍትሐዊ ውድድርን ለማረጋገጥ ያለመ ነው።

### 4.2.5. የኤክሳይስ ታክስ ማሻሻያ

ምንም እንኳን በቅርብ ዓመታት ውስጥ በርካታ የኤክሳይዝ ታክስ ማሻሻያዎች የተተገበሩ ቢሆንም፤ ከኢኮኖሚያዊ ለውጦች አንፃር ተጨማሪ ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ ነው። በስትራቴጂው የትግበራ ጊዜ የሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ ማሻሻያዎች ይተገብራሉ።

- **የኤክሳይዝ ታክስ ሕጎችን ማሻሻል፡-** በስትራቴጂው የትግበራ ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ማሻሻያ ይደረጋል። በዚህም በተወሰኑት ላይ የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔዎች እንዲሻሻሉ፣ አዳዲስ የኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልባቸው እንዲካተቱ እና በቁርጥ መጣኔ የሚገኙትም ከዋጋ ግሽበት ጋር እንዲጣጣሙ ይሰራል።
- **የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር ሥርዓትን መተግበር፡-** መንግሥት የኤክሳይዝ ታክስ ሕጉን በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግና ሕገ-ወጥ የዕቃዎችን/ሸቀጦችን ንግድ ለመቀነስ የሚያስችል የኤሌክትሮኒክስ የኤክሳይዝ አስተዳደር ሥርዓት (Excise stamp, tracking and tracing system) ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

### 4.2.6. የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሪፎርም እና ማሻሻያ

ባለፉት ስድስት ዓመታት አጠቃላይ የጉምሩክ የታሪፍ ደንብ እና የጉምሩክ ህጎች ላይ በርካታ መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጡ የሪፎርም እና የማሻሻያ ስራዎች ተከናውነዋል። ሆኖም በሀገር ውስጥ እየተከናወኑ የሚገኙ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች፣ አህጉራዊ የኢኮኖሚ ውህደቶች፣ የዓለም የንግድ ድርጅት አባልነት ወዘተ ከፍተኛ ለውጥ እና ዝግጅት የሚጠይቁ በመሆናቸው ተጨማሪ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ማድረግ ያስፈልጋል። ስለሆነም በስትራቴጂው የትግበራ ጊዜ ቀጣይ የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ማሻሻያ፣ የሱር ታክስ፣ የቀረጥና ታክስ ማበረታቻ እና ነጻ፣ የጉምሩክ አዋጅ፣ የጉምሩክ ደንብ እና ተያያዥ ህጎች የማሻሻል ስራዎች ይከናወናሉ።

## ሠንጠረዥ፡ ከ2017 እስከ 2020 የሚተገበሩ የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ማጠቃለያ

| የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች | የሪፎርሙ መነሻ ዓመት | የትግበራ ጊዜ እና ከየሪፎርሚ ሊገኝ የሚችል ገቢ (የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በመቶኛ) | | | | ድምር ተጨማሪ ገቢ (የታክስ ገቢ ከጠቅላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | ከ2017 እስከ 2020 |
| **የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች እና የውጭ ምንዛሪ ሪፎርም እና የኢኮኖሚ መንሰራራት ድምር ተጨማሪ ገቢ** | 0.36 | 1.00 | 2.60 | 3.60 | 4.00 | 4.00 |
| 1. የውጭ ምንዛሪ ሪፎርም እና የኢኮኖሚ መንሰራራት (Foreign Exchange Reform and Economic Recovery) | 0.00 | 0.20 | 0.40 | 0.80 | 1.00 | 1.00 |
| 2. የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ድምር ተጨማሪ የታክስገቢ | 0.10 | 0.80 | 2.20 | 2.80 | 3.00 | 3.00 |
| 2.1. የገቢ ግብር ሪፎርም | 0.00 | 00 | 0.40 | 0.40 | 0.60 | 0.60 |
| ሰንጠረዥ መሰረት ያደረገውና በስራ ላይ ያለውን የገቢ ግብር ስርዓትን ማሻሻል | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 |
| የታክስ ማበረታቻን ማሻሻል (ለምሳሌ ዝቅተኛ አማራጭ ታክስ MAT ተግባራዊ ማድረግ) | 0.00 | 0.00 | 0.40 | 0.40 | 0.60 | 0.60 |
| የቁርጥ ግብርን በማሻሻል የታክስ ስርዓቱን ቀላል ማድረግ | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 |
| ተፈርመው ሥራ ላይ የዋሉ የተደራራቢ ታክስ ማስቀረት ስምምነቶች እንደገና በመፈተሽ ማሻሻል፤ በታክስ ፖሊሲ መመሪያ ስር የዓለም ዓቀፍ ታክሶች ዩኒት ማቋቋም | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 |
| ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የተጣለ ታክስን ማሻሻል | 0.00 | -0.10 | -0.10 | -0.10 | -0.10 | -0.10 |
| ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ግብር ሪፎርም የሚታጣ ገቢ በዊዝ ሆልዲንግ ታክሶች ማካካስ | 0.00 | 0.10 | 0.10 | 0.10 | 0.10 | 0.10 |

| የታክስ ፖሊሲ ሪፎርም እና ማሻሻያ | የሪፎርሙ መነሻ ዓመት | የትግበራ ጊዜ እና ከየሪፎርሚ ሊገኝ የሚችል ገቢ (የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በመቶኛ) | | | | ድምር ተጨማሪ ገቢ (የታክስ ገቢ ከጠቅላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | ከ2017 እስከ 2020 |
| **2.2. የንብረት ታክስ ሪፎርም** | **0.00** | **0.10** | **0.20** | **0.30** | **0.30** | **0.30** |
| የንብረት ታክስ በተጣጣመ መልኩ በሀገር ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ | 0.00 | 0.10 | 0.20 | 0.30 | 0.30 | 0.30 |
| **2.3. የሞተር ተሽከርካሪ ዝውውር ታክስ** | **0.00** | **0.00** | **0.10** | **0.20** | **0.20** | **0.20** |
| የሞተር ተሽከርካሪ ዝውውርን ታክስ ማሻሻል | 0.00 | 0.00 | 0.10 | 0.20 | 0.20 | 0.20 |
| **2.4. የኤክሳይስ ታክስ ሪፎርም እና ማሻሻያ** | **0.00** | **0.40** | **0.40** | **0.80** | **0.80** | **0.80** |
| የኤክሳይስ ታክስ አስተዳደር ሥርዓትን መተግበር | 0.00 | 0.30 | 0.30 | 0.30 | 0.30 | 0.30 |
| የኤክሳይዝ ታክስ ተመኖችን ማሻሻል | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.10 | 0.10 | 0.10 |
| ለተወሰኑ ተመኖች የዋጋ ግሽበት ማስተካከል | 0.00 | 0.10 | 0.10 | 0.10 | 0.10 | 0.10 |
| በህጉ መሰረት የኤክሳይዝ ታክስ ከነዳጅ እንዲሰበሰብ ማድረግ | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.30 | 0.30 | 0.30 |
| **2.5. የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ** | **0.00** | **0.30** | **1.10** | **1.10** | **1.10** | **1.10** |
| በተመረጡ አገልግሎቶች ላይ የነበረው የተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ እንዲነሳ ማድረግ | 0.00 | 0.30 | 0.40 | 0.40 | 0.40 | 0.40 |
| በተዘጋጁ ምግቦች የነበረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እንዲነሳ ማድረግ | 0.00 | 0.00 | 0.10 | 0.10 | 0.10 | 0.10 |
| ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሆኑ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ ታክሱ መጣል | 0.00 | 0.00 | 0.10 | 0.10 | 0.10 | 0.10 |
| በህጉ መሰረት የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔ ስራ ላይ እንዲውል በማድረግ ታክሱ መሰብሰብ እንዲቻል ማድረግ | 0.00 | 0.00 | 0.50 | 0.50 | 0.50 | 0.50 |

| የታክስ ፖሊሲ ሪፎርም እና ማሻሻያ | የሪፎርሙ መነሻ ዓመት | የትግበራ ጊዜ እና ከየሪፎርሚ ሊገኝ የሚችል ገቢ (የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በመቶኛ) | | | | ድምር ተጨማሪ ገቢ (የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በመቶኛ) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | ከ2017 እስከ 2020 |
| **2.6. የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማሻሻያ** | **0.36** | **0.00** | **0.00** | **0.00** | **0.00** | **0.00** |
| የጉምሩክ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያዎች ማሻሻል | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 |
| የጉምሩክ ታሪፍ ስርዓቱ ቀላል እንዲሆን ማድረግ | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 |
| የሱር ታክስ እንዲቀር ማድረግ | 0.00 | 0.00 | 0.00 | -0.30 | -0.30 | -0.30 |
| የቀረጥና ታክስ ማበረታቻ እና ነጻን በመፈተሽና አላስፈላጊዎችን በማስቀረት የሚታጣውን ገቢ ማዳን | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.30 | 0.30 | 0.30 |
| የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ሥራ ላይ ማዋል | 0.36 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | 0.00 |

## 2.7. የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች

ዘመናዊ እና የታክስ መርሆችን በትክክል የሚከተል የታክስ አስተዳደር መሰብሰብ የሚገባውን የታክስ ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ያደርጋል። ይህ በታክስ ከፋዩ እና በአጠቃላይ በህብረተሰቡ ተቀባይነት ስለሚኖረው የታክስ አስተዳደሩ የሚከበር እና የሚፈራ እንዲሆን በማድረግ ታክሱ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ከማገዙ በተጨማሪ የታክስ መሰረቱ እንዲሰፋ እና ቀጣይነቱ እንዲረጋገጥ ያደርጋሉ። ከዚህ አንጻር በታክስ አስተዳደር ተቋሙም ሆነ በታክስ ከፋዩ ብዙ ርቀት መጓዝና በርካታ ስራዎችን መስራት የሚጠይቅ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዷል። ስለሆነም የታክስ አስተዳደሩን ለማዘመን የሚከተሉት ዋና ዋና የታክስ እና የጉምሩክ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ይከናወናሉ፡፡

- **የሪፎርም ዩኒት በገቢዎች ሚኒስቴር እና በጉምሩክ ኮሚሽን ማቋቋም፡-** የሪፎርም እና የማሻሻያ ስራዎች ጥብቅ አመራር በመስጠት እና ክትትል በማድረግ በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ በማድረግ የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት እንዲቻል ተጠሪነቱ በቀጥታ ለገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር እና ለጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር የሆነ የሪፎርም ዩኒት ይቋቋማል፡፡
- የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ያለበትን ደረጃ በመፈተሽ ደረጃውን ማሻሻል እና የTADAT ግምገማ በማካሄድ የታክስ አስተዳደር ስርዓቱን የማዘመን ስራዎች በመስራት የምዛና ውጤቱ በመጀመሪያ የዳሰሳ ምዘና ውጤት በስትራቴጂው የመጨረሻ ዓመት የትግበራ ጊዜ ቢያንስ በአንድ ደረጃ ከፍ እንዲል ይሰራል።
- **የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የመረጃ አያያዝ ስርዓትን ማሻሻል፡-** የተሟላ እና ትክክለኛ የታክስ ከፋይ መረጃን መያዝ ለታክስ አስተዳደር ዉጤታማነት ወሳኝ ነው፡፡ ይህ የታክስ አስተዳዳሩ ስለታክስ ከፋዮች የሶስተኛ ወገን መረጃ በቀላሉ እንዲፈትሹ እና በተለያዩ የመንግስት ተቋማት የመረጃ ፍሰት እንዲሻሻሉ በማስቻል የሚወሰኑ ውሳኔዎች መረጃን መሰረት ያደረጉና ተቀባይነት ያላቸው እንዲሆኑ ያግዛል፡፡ ሆኖም አሁን ላይ በፌደራልም ሆነ በክልል እና በከተማ አስተዳደር የገቢ ቢሮዎች ያለው የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ደካማ ነው፡፡ የመረጃ አያያዙ ወጥነት የሌለው፣ ጥቅል መሆኑ፣ በዘርፍ ወይም በንዑስ ዘርፍ፣ በመንግስትና በግል፣ ወዘተ የተደራጀ አይደለም፡፡ በመሆኑም በስትራቴጂው የትግበራ ጊዜ የታክስ አሰተዳደር ስርዓቱ ለማዘመን የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ ዲጂታል እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓቱን ዲጂታል ማድረግ ማለትም ስርዓቱን ከአውቶሜትድ ሲስተም (*ASYCUDA*) ወደ ኤሌክትሮኒክስ

ጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት (eCMS) ሙሉ በሙሉ እንዲሸጋገር ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በሚቀጥሉት አራት ዓመታት የጉምሩክ የታሪፍ አመዳደብ ሂደቱን በዲጅታል በማድረግ ግልጽነትን ለማረጋገጥ ይሰራል።

- የታክስ ከፋዮች የክትትልና ድጋፍ ማዕከላት ማሻሻል፤ ኮምፒዩተራይዝድ የአደጋ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት፤ የኦዲት፣ የስጋት እና የመረጃ አደረጃጀቶች አንዱ ከአንዱ ነጻ በሆነ አግባብ ማደራጀት፤ የብሔራዊ ክላላዊ መንግስታት እና የከተማ አስተዳደሮች የታክስ ገቢ አስተዳደር ስርዓትን ማዘመንና ማጣጣም፤ የገቢ ባለሥልጣኖች ለማጠናከር የሰው ኃይል ልማት ስትራቴጂ ማዘጋጀት እና ማጣጣም፤ የኤክሳይስ ታክስ አስተዳደር ቴክኖሎጂ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ ህግ-ወጥ የዕቃዎች ዝውውርን መቆጣጠርና ገቢን ማሳደግ፤ የህግ ተገዢነትን ለማሻሻል የሚያግዙ ስራዎች መለየትና መተግበር፤ ሀገር አቀፍ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ የሚሰራበት አደረጃጀት በመፍጠር ወጥ የሆነ የዕቃዎች እና የአገልግሎቶች ዋጋ መጠቀም፤ የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ታክስ የሚከፍሉበት የተለየ አደረጃጀት ማቋቋም፤ የመረጃ አስተዳደር ፖሊሲ እና አሰራር መዘርጋት፤ የተቋማት ቅንጅት ለመከታተል የሚያግዝ አደረጃጀት በመፍጠር በታክስ አስተዳደር የሚመለከታቸው ተቋማት የሚጠበቅባቸውን እንዲወጡ ማድረግ እና የጥናትና ምርምር አደረጃጀቱ በማጠናከር በታክስ አስተዳደር ላይ ብቻ በማተኮር በምርምር የታክስ አስተዳደር ችግሮችን መቅረፍ፣ ምርጥ ተሞክሮዎችና ልምዶች በመቀመር፣ አጠቃላይ የታክስ አስተዳደር ስርዓቱን የማጣጣም ምርምሮች በማካሄድና ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ፣ በመለየት እንደፈቱ የማድረግና ምርጥ ስራዎች በስፋት እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡

እነዚህን የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች በመተግበርና የታክስ አስተዳደር ስርዓቱን በማዘመን በስትራቴጂው የመጨረሻ ዓመት የትግበራ ጊዜ በአጠቃላይ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በ2.9 በመቶኛ እንዲያድግ ወይም እንዲጨምር የሚሰራ ሲሆን፤ በስትራቴጂው የሚሰሩ ዋና ዋና ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች በሚከተለው ሰንጠረዝ ቀርበዋል፡፡

**ሠንጠረዥ፡ በታክስ አስተዳደር ከ2017 እስከ በ2020 የሚተገበሩ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ማጠቃለያ**

| የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች | የሪፎርሙ መነሻ ዓመት | የትግበራ ጊዜ እና ከየሪፎርሚ ሊገኝ የሚችል ገቢ (የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በመቶኛ) | | | | የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2017 — 2020 |
| **3. የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ዝርዝር ተግባራት** | 0.00 | 0.20 | 0.60 | 0.90 | 1.20 | 2.90 |
| የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን የታክስ ሪፎርም ዩኒት ያቋቁማሉ | | | | | | |
| የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን የዲጂታይዜሽን ደረጃቸውን በመፈተሽ አስፈላጊውን ማሻሻያ ለማድረግ የዲጂታይዜሽን የራስ ምዘና በየጊዜው ያደርጋሉ | | | | | | |
| የገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ አስተዳደር ጤናማነት ምዘና (TADAT) በማድረግ ክፍተቶችን በማስተካከል ደረጃውን በማሻሻል አገልግሎቱን ያዘምናል | | | | | | |
| የገቢዎች ሚኒስቴር የዓለም አቀፍ ታክስ የማስተዳደር ዝግጁነት በሚመለከት አደጋ ለመቀነስ የዓለም አቀፍ ታክስ አስተዳደር ጥንካሬ (Framework for International Tax Administrative Strengthening) ዝግጁነት ፍተሻ ያደርጋል፤ የዓለም አቀፍ ታክሶች ክትትል የኒት በማደራጀት ጥብቅ ክትትል ያደርጋል፤ | | | | | | |
| የታክስ ተገዥነት ስጋት አስተዳደር ማዕቀፍ (Compliance Risk Management) መገንባት | | | | | | |
| የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና እና መረጃ አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል (አይታስ፣ ኢ-ኦዲት ማስተዋወቅ፣ ኢ-ስጋት ግምገማ፣ ወዘተ) | | | | | | |
| የታክስ ከፋዮች የመረጃ እና ድጋፍ ማዕከልን ማሻሻል | | | | | | |
| ዘመናዊ በኮምፒዩተር የተደገፈ የስጋት አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት | | | | | | |
| ኦዲትን፣ ስጋትን፣ ኢንተለጀንስ እና ምርመራን አደረጃጀቶች አንዱ ከአንዱ ነጻ በሚሆንበት አግባብ ማደራጀት | | | | | | |
| የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት እና ከተማ አስተዳደሮች የታክስ ገቢ የመሰብሰብ አቅም ማጠናከር | | | | | | |

| የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች | የሪፎርሙ መነሻ ዓመት | የትግበራ ጊዜ እና ከየሪፎርሙ ሊገኝ የሚችል ገቢ (የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በመቶኛ) | | | | **የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በመቶኛ** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2017 — 2020 |
| የሰው ኃይል ልማት ስትራቴጂ ማዘጋጀት፤ በዚህም የሰው ኃይል አቅም መገንባት | | | | | | |
| አስፈላጊውን አደረጃጀት በመዘርጋት የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር መተግበር | | | | | | |
| በፈቃደኝነት ታክስ የመክፈል ልምድ ማሻሻል | | | | | | |
| የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን የሚሰሩበት ሀገር አቀፍ የትክክለኛ ዋጋ ስሌት የሚሰራ መዋቅር መፍጠር | | | | | | |
| የመንግስትየልማት ድርጅቶች  ታክስ የሚከፍሉበት ቢሮ መክፈት | | | | | | |
| የመረጃ አስተዳደር ፖሊሲ ማዘጋጀት | | | | | | |
| በተቋማት መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከታተል አደረጃጀት መፍጠር | | | | | | |
| በስራ ላይ የሚገኝ የሽያጭ መሳሪያ በዘመናዊ እና ከገቢዎች ሚኒስቴር የመረጃ ቋት ጋር በኢንተርኔት ማገናኘት በሚያስችል መልኩ ማሻሻል | | | | | | |
| ትክክለኛ አገልግሎት ለመስጠት እና ወቅቱ የጠበቀ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የመረጃ ሳይነስ ማልማት | | | | | | |
| የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን (የፌዴራል፣ የክልል፣ የከተማ አስተዳደር ወዘተ) ለማሻሻልና ለማጣጣም የጥናትና ምርምር መምሪያን ወደ የአገር ውስጥ ታክስና ጉምሩክ ታሪፍ ኢንስቲትዩት በማሻሻል እንደገና ማዋቀር። ይህ አሁን ያለውን የገቢዎች ሚኒስቴር የክልል ድጋፍ ደረጃጀትን ሊያካትት ይችላል። | | | | | | |
| የገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ አስተዳደርን ለማጣጣም ስትራቴጂ በመንደፍ ይሰራል፤ የታክስ አስተዳደር ስርዓቱ በሀገር ደረጃ ወደ ዘመናዊ ደረጃ ከፍ ማለቱን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል። ይህ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት እና የከተማ አስተዳደሮች የታክስ አስተዳደር ስርዓታቸውን ለማዘመን የታክስ አስተዳደራቸውን ለመገምገም እገዛ ማድረግን ሊያካትት ይችላል (TADAT፣ Digitization Maturity፣ CRM፣ ወዘተ) | | | | | | |

## 3.3. ታክስ ያልሆኑ የገቢ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች

ታክስ ያልሆኑ የገቢ አሰባሰብን በዘላቂነት ለማጎልበት እና አስተዳደርን ለማሻሻል መንግስት የሚከተሉትን ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ይተገብራል፡፡

- **የክፍያ ተመንን በመደበኛነት ማሻሻል**፡- የፌደራል መንግስት እና ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት እና ከተማ አስተዳደሮች ለሚጧቸው የህዝብ አገልግሎቶች እና ዕቃዎች የሚያወጡት የዋጋ ተመን በየጊዜው ወቅታዊ ያደርጋሉ፡፡
- **የክትትል እና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓትን ማጠናከር፡-** መንግሥት የተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ አስተዳደር ስርዓትን በመተግበር የሪፖርት ማቅረቢያ እና የታክስ ያልሆኑ ገቢዎችን ለመቆጣጠር የሚረዱ ዘዴዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
- **የመንግስት የልማት ድርጅቶች አስተዳደርን ማዘመን**፡- የመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጭነትን ለማረጋገጥ የአስተዳደር እና የአመራር አቅምን የሚያሳድጉ ሪፎርሞችና ማሻሻያዎችን ይተገበራሉ፡፡
- **በተፈጥሮ ሀብት ያለውን የመንግስት ድርሻ መከለስ፡-** በተፈጥሮ ሀብት ፍለጋና ማውጣት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያሉ የፍትሃዊነት ድርሻ ላይ ማሻሻያ ይደረጋል፡፡
- **ሌሎች ታክስ ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን መለየት**፡- መንግስት ተጨማሪ ታክስ ያልሆኑ የገቢ ምንጮች በጥናት በመለየት ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

# 4.የስኬት ምክንያቶች እና የትግበራ ስጋቶች

## 4.3. የስኬት ምክንያቶች

### 4.3.1. በየደረጃው ከፍተኛ የሆነ የአስፈፃሚ አካላት ቁርጠኝነት መኖር

ስትራቴጂውን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ በሁሉም የመንግስት እርከኖች ብሎም በተለያዩ የባለ ድርሻ አካላት (የመንግስት ተቋማትን ጨምሮ) ያለው የማስፈፀም አቅምና ፍላጎት በጣም ወሳኝ ነው፡፡

**የአስፈፃሚ አካላት ቁርጠኝነት**፡ በከፍተኛ ደረጃ ያሉ የአስፈፃሚ አካላት የጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤትን ጨምሮ ቁርጠኝነትና ቅንጅት በስትራተጂው የተቀመጡትን ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች በተቀመጠለት የጊዜ ገድብ በትክክል ለመተግበር እና የታለመለትን ዓላማ እዲያሳካ በማድረግ ጉልህ ሚና ይኖረዋል፡፡ ይህም የታክስ ሪፎርሞችን እና ማሻሻያዎችን በአግባቡ እንዲተገብሩ የሚያስችል በክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር ከፍተኛ የማክሮ ኢኮኖሚ አማካሪ የሚመራ ብሔራዊ የታክስ ሪፎርም ታስክ ፎርስ ተቋቁሟል፡፡

የተቀናጀ የልማት አጋሮች የአቅም ግንባታ ድጋፍ በተለይ ለታክስ ፖሊሲ አውጪውና ለታክስ ሰብሳቢው አካል ስትራቴጂውን ለመተግበር ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡ ይህ ድጋፍ የፖሊሲ እና አስተዳደራዊ ሪፎርሞችን እና ማሻሻያዎችን የማስፈጸም አቅምን ያሳድጋል፡፡ በተጨማሪም የልማት አጋሮች የስትራቴጂውን ትግበራ፣ ክትትል እና ግምገማ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡

እንደ የዓለም የገንዘብ ድርጅት እና የዓለም ባንክ ያሉ ተቋማት የልምድ ልውውጥ ለሚመለከታቸው የአስፈፃሚ አካላት በማዘጋጀት ስትራቴጂውን በተሳካ ሁኔታ ለመተግበር ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

### 4.3.2. ግብር ከፋዮች

የግብር ከፋዩ ተሳትፎና ትብብር ለስትራቴጂው ትግበራ ስኬት ወሳኝ ነው፡፡ ግብር ከፋዮችን በስትራቴጂው እና በአተገባበሩ ሂደት ውስጥ ማሳተፍ ስትራቴጂው ውጤታማ እንዲሆንና የታክስ ተገዢነትን ከፍ እንዲል በማድረግ የታክስ ስርዓቱን ያጠናክራል፡፡

### 4.3.3. በቅርብ ጊዜ የተደረጉ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች

የመንግስት የፕራይቬታይዜሽን መርሃ ግብር ተወዳዳሪ የሆነ የገበያ መዋቅርን ለመፍጠር፣ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳደግ ያለመ ነው፡፡ እነዚህ መጠነ ሰፊ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች የግል ኢንቨስትመንትን እና ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦ በማጎልበት የገቢ አሰባሰብን ያሳድጋሉ፡፡

## 4.4. የትግበራ ስጋቶች

### 4.4.1. ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች

ኢትዮጵያ የአፍሪካ የንግድ ቀጠና ስምምነት በመፈረሟ ወደ ትግበራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ትገኛለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን በሂደት ላይ ስትሆን፤ እነዚህ ሁለት የንግድ ትብብር ስምምነቶች መተግበር የየራሳቸው የሆነ ስጋት ወይም በጎ ዕድሎች የሚፈጥሩ በመሆናቸው ዕድሎችን አሟጦ ለመጠቀም እና ስጋቶችን ለመቀነስ ካልተቻለ በስትራተጂው አተገባበር ላይ ወይም በሚጠበቁ ውጤቶች ላይ አሉታዊ ሚና ሊኖረው እንደሚችል ይገመታል፡፡

### 4.4.2. ደካማ የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መሻሻል ቢታይም፣ የኢትዮጵያ የየኢንፎርሜሽንና ቴክኖሌጂ መሠረተ ልማት ወደ ኋላ በመቅረቱ የታክስ አስተዳደርን ዲጂታላይዝ ለማድረግ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ክፍተት መፍታት ለታክስ አስተዳደር ሪፎርም እና ማሻሻያ ትግበራ ላይ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡

### 4.4.3. የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት

**ከፍተኛ የመንግስት እዳ እና ደካማ የወጪ ንግድ**፡- ከፍተኛ የሆነ የመንግስት ዕዳ ጫናና የዕዳ ክፍያ፣ በስትራቴጂ ውስጥ የተዘረዘሩትን የገቢ ዕቅዶች ለማሳካት እንደስጋት ተቀምጠዋል፡፡ የውጭ ምንዛሪ እጥረት የስትራቴጂውን ዕቅዶች ከማሳካት አኳያ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህን የስኬት ተግዳሮቶች በመፍታት እና ለትግበራ ስጋቶች ቅነሳ ስልቶችን በመተግበር የስትራቴጂውን ውጤታማነት በማጎልበት የገቢ ማሰባሰብ ግቦችን ከአጠቃላይ የልማት ግቦች ጋር በማጣጣም ማሳካት ተገቢ ይሆናል፡፡

# 5. የስትራቴጂው ፍኖተ ካርታ፣ ክትትል እና ግምገማ ማዕቀፍ

## 5.3. የስትራቴጂው ፍኖተ ካርታ

የስትራቴጂውን የትግበራ ፍኖተ ካርታ በመካከለኛ ዘመን የስትራቴጂውን የትግበራና አፈጻጸም ሂደት ለመምራት የተነደፈ ስትራቴጂክእቅድ ሆኖ ያገለግላል። ይህ ፍኖተ ካርታ የፖሊሲ አወጣጥ እና አፈፃፀም ተለዋዋጭ እና ተደጋጋሚ ባህሪን በመገንዘብ የተለያዩ ተግባራትን ለማቀድ እና ለማስፈፀም የተቀናጀ አቀራረብ ይኖረዋል። ስለሆነም የሚከተሉት ንዑስ ዓላማዎች ይኖሩታል።

- **ቁልፍ ተግባራትን መለየት**፦ ፍኖተ ካርታው ለስትራቴጂው ስኬታማ ትግበራ አስፈላጊ የሆኑትን ወሳኝ ተግባራት ይዘረዝራል፣ አላማውን ለማሳካት በሚያስፈልጉት ማሻሻያዎች ላይ አቅጣጫ ይሰጣል።
- **ክንዋኔዎችን መከታተል**፦ ግልጽ የሆኑ ወሳኝ ክንውኖችን እና የክትትል ስልቶችን በማቋቋም ፍኖተ ካርታው ወደ ስትራቴጂው ትግበራ የሚደረገውን ሂደት መከታተልን ያመቻቻል። ይህ የትግበራ ፍኖተ-ካርታ ባለድርሻ አካላት ውጤታማነት ለመለካት እና እንደ አስፈላጊነቱ አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል።
- **የተለያዩ የባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ትግበራን መከታተልና ማረጋገጥ**፦ በሁሉም የመንግስት እርከኖች ያሉ ባለድርሻ አካላት ስትራቴጂካዊ ቅንጅት በፍኖተ ካርታው ውስጥ ቅድሚያ ተሰጥቶታል። በሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት መካከል ትብብርን እና ግንኙነትን በማጎልበት ጥረቶችን በማሳለጥ  አጠቃላይ የአተገባበሩን ውጤታማነት ያረጋግጣል።
- **ተግዳሮቶችን እና እድሎችን መለየትና የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረብ**፦ ፍኖተ ካርታው ባለድርሻ አካላት ከስትራቴጂው ትግበራ ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ ተግዳሮቶችን እና እድሎችን ለመገመት ይረዳል። እነዚህን  ቀደም ብሎ በመለየት፣ ባለድርሻ አካላት አደጋዎችን ለመቀነስ እና እድሎችን ለመጠቀም ቀድሞ በማቀድና፣ በዚህም የስኬት እድሎችን ከፍ በማድረግ ስትራቴጂው ስኬታማ እንዲሆን ጥረት ያደርጋል።

በአጠቃላይ ፍኖተ ካርታው የስትራቴጂው አተገባበርን በመዳሰስ፣ በተቀናጀ አቀራረብ ስትራቴጂው በገቢ አሰባሰብ እና ሀገራዊ ልማት ግቦች ላይ ያለውን ተጽእኖ የሚያጎለብት ማዕቀፍ እንዲኖር ይረዳል።

ስለሆነም ስትራቴጂውን ለመተግበር የሚያስፈልጉት ቁልፍ እርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ሀ) የባለድርሻ አካላት ልየታ

የባለድርሻ አካላት ልየታበስትራቴጂው ትግበራ ውስጥ የመጀመሪያው ተግባር ይሆናል፡፡ ግብር ከፋዮች እና የልማት አጋሮችን ጨምሮ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካላት ለስትራቴጂው ትግበራ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የገቢዎች ሚኒስቴር ግንባር ቀደም ይሆናሉ፡፡ ስለሆነም የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በመለየት የእያንዳንዱን ባለድርሻ አካላት ሚና እና ኃላፊነት ማሳወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ በስትራቴጂው አተገባበር ውስጥ ያሉትን ባለድርሻ አካላት ማትሪክስ ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ፡ የባለድርሻ አካላት ልየታ

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት | በስትራቴጂው ትግበራ ውስጥ ያሉ ሚናዎች |
|---|---|---|
| 1. | መንግስት | ▪ መንግስት የስትራቴጂውን ትግበራ በማስተባበር እና በመምራት ላይ ይሆናል. ይህንንም ለማድረግ መንግስት የክልል መንግስታትን ጨምሮ የተለያዩ የመንግስት አካላትን ሚና እና ኃላፊነት የሚያሳይ ግልፅ የአስተዳደር መዋቅር አውጥቷል፡፡ |
| 2. | የንግዱ ማህበረሰብ | ▪ በስትራቴጂው ትግበራ ውስጥ ካሉት ዋና ባለድርሻ አካላት አንዱ እንደመሆኑ መጠን፣ መንግስት የስትራቴጂውን ሰፊ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች በሚመለከት መደበኛ እና ወቅታዊ መረጃ በመስጠት፤ እንዲሁም በስትራቴጂው ትግበራ ላይ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ችግሮችን ለመፍታት ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር በቅርበት ይሰራል፡፡ . |
| 3. | የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች | ▪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በስትራቴጂው ዝግጅት እና አተገባበር ቁልፍ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በሚቀጥሉት አራት ዓመታት በቀረቡት የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ላይ አስተያየት ለመቀበል ከሚመለከታቸው የሲቪል ማህበራት ጋር የተለያዩ የምክክር መድረኮች ይዘጋጃሉ፡፡<br>▪ ይህም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በስትራቴጂው ላይ በተገለጸው መሰረት የስትራቴጂው ስለመፈጸሙ መንግስትን ይከታተላሉ፡፡ ሁለተኛ፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ስትራቴጂውን ለመከታተል እና ለመገምገም እና ለተሃድሶዎቹ ተፅእኖ ግምገማ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ |
| 4. | ሁሉም የልማት አጋሮች | ▪ መንግስት ለተለያዩ ፈጻሚ አካላት የአቅም ግንባታ እና ስትራቴጂውን በትክክል ለመተግበር እንዲቻል በገንዘብ በመደገፍ ስትራቴጂውን በብቃት በመተግበር ረገድ መንግስታት፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ሌሎች የልማት አጋሮች የሚጫወቱትን ወሳኝ ሚና ይገነዘባል፡፡ ስለዚህ፣ መንግሥት በስትራቴጂው ላይ በየጊዜው ማሻሻያዎችን ለልማት አጋሮች ይሰጣል፤ የውይይት መድረኮችን ያዘጋጃል፡፡ |

ማስታወሻ፡ ስትራቴጂው እየተተገበር ሲሄድ የባለድርሻ አካላት ማትሪክስ ማስተካካያ ሊደረግበት ይችላል፡፡

## ለ) ስትራቴጂውን ለተለያዩ የባለ ድርሻ አካላት ማስተዋወቅ

የስትራቴጂው ውጤታማ ትግበራን ለማረጋገጥ መንግሥት የስትራቴጂውን ዓላማ፣ ዒላማ ተመልካቾችን፣ የመገናኛ መስመሮችን፣ የግንኙነት ድግግሞሽን እና የግምገማ ዘዴዎችን የሚገልጽ ግልጽ የግንኙነት ስትራቴጂ ያዘጋጃል:: ይህም መንግስት ስትራቴጂውን ከመተግበር አኳያ ሰፊ የህዝብ ድጋፍ እንዲያገኝ ያስችለዋል:: የስትራቴጂው የማስተዋወቂያ ስትራቴጂ የሚከተሉት ናቸው::

1. **ዓላማ**፡- የማስተዋወቂያ ዓላማው ለስትራቴጂው ሰፋ ያለ ሕዝባዊ ግንዛቤን ለመገንባት ነው:: በታክስ ፖሊሲ እና አስተዳደራዊ ለውጥ ላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለመፍጠርም ያለመ ነው::

2. **ባለድርሻ አካላት**፡- የስትራቴጂው ታሳቢ የሚያደርገው ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ማለትም አጠቃላይ ህዝብ፣ ግብር ከፋዮች/የንግድ ማህበረሰብ፣ አለም አቀፍ የልማት አጋሮች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የተለያዩ የመንግስት አካላት ናቸው::

3. **ስትራቴጂውን የማስተዋወቂያ መንገዶች**፡- የተለያዩ እና ተደራሽ የመገናኛ አውታሮችንማህበራዊ ሚዲያ፣ ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ ህዝባዊ ዝግጅቶች ጨምሮ የአከባቢ ቋንቋዎችን በመጠቀም ስትራተጂውን ለህዝብ ይተዋወቃል::

4. **ስትራቴጂውን በመደበኛ ለህዝብ ማስተዋወቅ**፡- በስትራቴጂ ላይ መደበኛ እና ወቅታዊ ትግበራና አፈጻጸም በተለዩት የመገናኛ ኣውታሮች ለህዝብ እንዲደርሱ የደረጋል:: በዚያ ላይ የስብሰባ መድረኮችእና ህዝባዊ ዝግጅቶች በዓመት ሁለት ጊዜ እንዲዘጋጁ ይደረጋል::

5. **ስትራቴጂውን የማስተዋወቂያ መንገዶች በመደበኝነት መገምገም**፡- በመደበኛነት ስትራቴጂውን የማስተዋወቂያ መንገዶችን በመገምገም ማሻሻያ በማድረግ ለስትራተጂው ትግባራና አፈጻጸም ጉልህ ሚና እንዲኖረው ይደረጋል::

## ሐ) ስትራቴጂውን መተግበር

ይህ ስትራቴጂው ወደ ትግበራ የሚገባበት ደረጃ ነው። በዚህ ደረጃ ላይ የትግበራ ቅድመ ትግበራ ተከተል እንደሚከተለው ነው።

- ***በባለሙያ ደረጃ የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፡-*** የስትራቴጂው የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነድ እንደተጠናቀቀ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅትን ለማመቻቸት የባለሙያ ደረጃ የምክክር መድረክ ይዘጋጃል። እነዚህ የምክክር መድረኮች በተለያዩ የባለድርሻ አካላት የሚደረጉ የትግበራ እንቅስቃሴዎችን ለማጣጣም እና ስትራቴጂውን በተስማሙበት የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ለማስፈፀም ይረዳሉ።
- **የባለድርሻ አካላት ስብሰባዎች፡-** የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን የትግበራ እንቅስቃሴዎች ለማስተባበር መደበኛ የባለድርሻ አካላት መድረኮች ይዘጋጃሉ። እነዚህ መድረኮች ጥረቶችን ለማስተባበር እና በመደበኛነት በየሩብ ዓመቱ እንቅስቃሴዎችን ለመገምገም ዕድል ይፈጥራሉ።
- ***ለሚመለከታቸው የባለድሻ አካላት ኃላፊነቶችን መመደብ፡-*** ግልጽ የሆነ የሪፖርት ማቅረቢያ እና የግንኙነት ዘዴዎች ለእያንዳንዱ ባለድርሻ አካላት በግልጽ ይቀመጣሉ። ይህ ስትራተጂውን በመተግበር ላይ ለሚሳተፉ የተለያዩ አካላት በተሰጡ ሚናዎች እና ተግባራት ውስጥ ተጠያቂነትን እና ግልፅነትን ያረጋግጣል።
- ***የህግ መደንገግ ሥራ፡-*** የስትራተጂውን ትግበራ ለመደገፍ አስፈላጊ የሆኑ የህግ ማዕቀፎች እና ደንቦች ይደነገጋሉ። ይህ የህግ ማዕቀፉ በስትራቴጂክ ሰነዱ ውስጥ ከተዘረዘሩት አላማዎች እና ስትራቴጂዎች ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥን ያካትታል።
- ***ስትራቴጂውን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ማፅደቅ፡-*** ስትራተጂውን በሁሉም የመንግስት ስራ አስፈጻሚ አካላት ለመተግበር እንዲቻል በሚኒስትሮች ምክር ቤት በማስጸደቅ ስራ ላይ እንዲውል የማድረግ ስራ ይካሄዳል።
- ***ስልጠና ማመቻቸትና ማዘጋጀት፡-*** አቅምን ለማጎልበት እና በስትራተጂው ስር የወጡትን አዳዲስ ፖሊሲዎችና አስተዳደራዊ ሪፎርሞችን እና ማሻሻያዎችን ለመረዳት የሚያስችል አጠቃላይ የስልጠና መርሃ ግብሮች በአገር ዉስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ይከናወናሉ። ይህ ስልጠና ወጥነት ያለው የመልእክት ልውውጥ እና ግንዛቤን ለማረጋገጥ ከመግባቢያ ስትራተጂ ጋር ሊጣመር ይችላል።
- ***የስርዓት ለውጦችን ማቀድ፡-*** በነባር ስርዓቶች እና ሂደቶች ላይ አስፈላጊ ለውጦች የስትራተጂው መስፈርቶችን ለማሟላት ታቅደው ተግባራዊ ይሆናሉ። ይህ በገቢ

አስተዳደር ውስጥ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት፣ የሶፍትዌር ሥርዓቶች እና የአሠራር ሂደቶች ማሻሻያዎችን ሊያካትት ይችላል።

- ***መደበኛ ግምገማዎችን ማመቻቸት***:- የስትራተጂው የመነሻ፣ የአጋማሽ እና የመጨረሻ ጊዜ ግምገማዎች መሻሻልን ለመገምገም፣ ተግዳሮቶችን ለመለየት እና የስትራቴጂውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ማስተካከያዎችን ለማድረግ አስቀድሞ በተገለጹ ክፍተቶች ውስጥ ይከናወናሉ። እነዚህ ግምገማዎች ውሳኔ አሰጣጥን ያሳውቃሉ እና ከ ስትራተጂው አጠቃላይ ግቦች ጋር መጣጣምን ለመጠበቅ ይረዳሉ።

## 5.4. የክትትል እና ግምገማ ማዕቀፍ

**የስትራቴጂው ውጤታማ ትግበራን ለማረጋገጥ ጠንካራ የክትትልና የግምገማ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ወሳኝ ነው።** የክትትል እና የግምገማ እቅዱ አፈጻጸምን ለመገምገም እና የስትራቴጂውን ተጽእኖ ለመገምገም መሰረት ሆኖ ያገለግላል። የክትትልና የግምገማ እቅድ ዋና ዋና አላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. **የስትራቴጂውን አፈጻጸም መከታተል**:- በስትራቴጂው ውስጥ የተዘረዘሩ ተግባራትን አፈፃፀም ሂደት መከታተልን ያመቻቻል፤ ይህም ወሳኝ ክንውኖች በተመደበው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ስትራቴጂውን ያረጋግጣል።
2. **ለባለ ድርሻ አካላት ስለ ስትራቴጂው ግንዛቤ መፍጠር**:- መደበኛ የክትትልና የግምገማ ተግባራት በስትራቴጂው ውስጥ ለሚሳተፉ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ስለ ስትራቴጂው ትግበራና አፈጻጸም፣ በቂ ግንዛቤ መስጠትና ግልጽነት ብሎም ተጠያቂነትን ማጎልበት።
3. **በብሄራዊ የመካከለኛ ዘመን ስትራቴጂ ዉስጥ የተካተቱ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችንና ሂደቶችን መገምገም**:- መደበኛ ግምገማ በማድረግ፣ በስትራቴጂው ስር የተተገበሩ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችን፣ ስርዓቶችን እና ሂደቶችን ውጤታማነት በመገምገም፣ ተግዳሮቶችን እና ማሻሻያዎችን ይለያል።
4. **በአስፈጻሚ አካላት መካከል ትብብርና መግባባት እንዲጎለብት ማድረግ**:- በሚመለከታቸው የተለያዩ አስፈጻሚ አካላትመካከል የሂደት ሪፖርቶችን መጋራት ትብብር እና ቅንጅትን ያበረታታል፤ ይህም ለስትራቴጂው ትግበራ የተቀናጀ አካሄድን ያመቻቻል።

በስትራቴጂው አጠቃላይ የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ውስጥ በገንዘብ ሚኒስቴር የሚመራ ራሱን የቻለ የክትትልና ግምገማ ዩኒት ተቋቁሟል፡፡ የዩኒቱ ኃላፊነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡፡ እነዚህም፡-

- የስትራቴጂውን ትግበራና አፈጻጸም ብሎምተፅእኖን ለመገምገም የክትትል እና የግምገማ ስራዎችን ማካሄ፤
- በስትራቴጂው ትግበራ በቀጥታ የሚመለከታቸው ተቋማት የገቢዎች ሚኒስቴርን እና የጉምሩክ ኮሚሽንን ጨምሮ ድጋፍ መስጠት፤
- በትግበራና አፈጻጸም ሂደት ላይ ለመወያየት እና ችግሮችን ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ የግምገማ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት
- የክትትልና የግምገማ ሥራዎችን ግኝቶች የሚገልጹ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት፤ እና
- በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ላይ ጥረቶችን በማስተባበር የስትራቴጂው ትግበራን ማሳለጥ፤

ይገኙበታል፡፡

## 5.5. ስትራተጂውን ለመተግበር የተቀረጸ አደረጃጀት


ይህንን ወሳኝ ብሄራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራተጂ ትግበራ በተቀናጀ መልኩ እንዲከታተል በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽቤት አማካኝ ነት ብሄራዊ የታክስ ማሻሻያ ግብረ ሃይል ተቋቁሟል፡፡ ይህ ግብረ ሃይልበተለያዩ የመንግስት እርከኖች የሚንቀሳቀሱ ሶስት የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያቀፈ ይሆናል፡፡

- **የባለሙያዎች ቡድን፡-** የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን እና የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ካሉ የመንግስት አካላት የተውጣጡ ባለሙያዎችን ያቀፈ ቡድን የስትራቴጂውን ትግበራና አፈጻጸም ይከታተላል፡፡ ይህ ቡድን የባለድርሻ አካላትን የተሳትፎ መድረኮችን የማደራጀት፣ ለስትራቴጂው ግብረ መልስ እና ግብአት የማሰባሰብ እና በመንግስት ኤጀንሲዎች ውስጥ የማሻሻያ ስራዎችን የማስተባበር ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም፣ የታቀዱትን ማሻሻያዎች አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፡፡ የባለሙያዎች ቡድኑ ቁልፍ በሆኑ ተግዳሮቶች እና በትግበራ ሂደት ላይ ለመወያየት እና

ለቴክኒክ ኮሚቴው መደበኛ የስራ ሂደት ሪፖርቶችን በማዘጋጀት በየሁለት ሳምንቱ እየተገናኘ ትግበራንና አፈጻጸምን ይገመግማል።

- **ብሔራዊ የታክስ ሪፎርም ቴክኒክ ኮሚቴ፡-** የቴክኒክ ኮሚቴው የሚመራው በገንዘብ ሚኒስቴር የታክስ ፖሊሲ መምሪያ ነው። የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከገቢዎች ሚኒስቴር እና ከኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የተውጣጡ የስራ ኃላፊዎች ናቸው። ይህ ኮሚቴ በየተቋማቱ ከሚቋቋሙ የሪፎርም ዩኒቶች በየተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች ጸድቀው የቀረቡትን ሪፖርቶች በመገምገም በዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ በመወያየት ለታስክ ፎርሱ የውሳኔ ሃሳቦችን ያቀርባል። የቴክኒክ ኮሚቴው በየሳምንቱ እየተሰበሰበ ያለውን ሂደት ለመገምገም እና በአፈጻጸም ላይ መመሪያ ይሰጣል።
- **ብሔራዊ የታክስ ሪፎርም ታስክ ፎርስ፡-** ታስክ ፎርሱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍተኛ የማክሮ ኢኮኖሚ አማካሪ ነው። ታስክ ፎርሱ የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ፣ የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ ሁለት የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ እና የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነርን ያካተተ ነው። ታስክ ፎርሱ ስትራቴጂው በትክክል እንዲተገበር በማድረግ የሚጠበቀውን ውጤት የማስገኘት ሀገራዊ ኃላፊነት የተሰጠው ሲሆን፤ በወር ሁለት ጊዜ ስብሰባ በማካሄድ አፈጻጸሙን ይከታተላል አመራርም የሚሰጥ ነው።

ምስል 6.1. የስትራቴጂው የአስተዳደር መዋቅር



# 6. ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ በተለይ እ.ኤ.አ ከ2004-2019 ባለው ጊዜ ውስጥ በአማካይ በዓመት ከ 10 በመቶ በላይ የሃገር ዉስጥ ምርት ዕድገት በማስመዝገብ ፈጣን የሚባል የኢኮኖሚ ለውጥ አስመዝግባለች፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ በቀጣናው ፈጣን ኢኮኖሚ እያስመዘገቡ ካሉት አንዷ ነበረች፡፡ ይሁን እንጂ ከ2020 ጀምሮ በተለያዩ ምክንያቶች እንደ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በተቀሰቀሰው ግጭት፣ በደቡብ እና በምስራቅ ኢትዮጵያ በተከሰተው የዝናብ እጥረትና ድርቅ፣ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና በዩክሬን ጦርነት ምክንያት የዕድገት መቀዛቀዝ ታይቷል፡፡ የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ተከትሎ በቀጠናው እድገቱ ደካማ ነበር፡፡ በኢትዮጵያ በ2020 አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት 6 በመቶ አካባቢ ተመዝግቧል፡፡ ይህ አሁንም ከሌሎች በቀጠናው ከሚገኙ ሀገራት ጋር ሲወዳደር በአንፃራዊነት ፈጣን ዕድገት ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ እ.ኤ.አ. በ2021 በሁሉም ክፍላተ አህጉራትና ቀጠና በሚባል ደረጃ አጠቃላይ የሃገራት ምርት በአንጻራዊነት ከወረርሽኙ ማገመም ችለዋል፡፡ ምንም እንኳ የሰሜኑ ጦርነት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ቢያስከትልም ኢትዮጵያ በቀጠናው ፈጣን የሚባል የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ ችላለች፡፡

ይሁን እንጂ ኢኮኖሚው አሁንም በርካታ ፈተናዎች የተጋረጡበት ሲሆን ከእነዚህም መካከል ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት፣ እያደገ የመጣው የመንግስት የበጀት ጉድለት፣ የመንግስት ከፍተኛ የዕዳ ጫና፣ ከፍተኛ የሥራ አጥነት ችግር፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እና የኤክስፖርት ዘርፍ ደካማ መሆን በአጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ይጠቀሳሉ፡፡ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት፣ በዝቀተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያለውን በተለይ ደግሞ ተቀጣሪው ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጥሯል፡፡ ይህ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች በተከሰተው ድርቅ እና በሰሜን በተከሰተው ግጭት፣ የሀገር ውስጥ አቅርቦት ሰንሰለትን ክፉኛ አስተጓጉሏል፡፡

እያደገ የመጣውን የአገሪቱን የወጪ ፍላጎት ለማሟላት ዘላቂ የሀገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጮች ለማጎልበት የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡ ይህንንም ለማሳካት መንግስት ከ2017 በጀት ዓመት ጀምሮ እስከ 2020 ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ብሄራዊ የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር አዘጋጅቷል፡፡ ስትራቴጂው የታክስ ፖሊሲን፣ የታክስ አስተዳደርን እና የህግ ማዕቀፉን በማቀናጀት ሁለንተናዊ አካሄድን ይከተላል፡፡ ስለዚህ ስትራቴጂው በሚቀጥሉ

አራት ዓመታት ውስጥ የሚተገበሩትን ቁልፍ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ጉዳዮችን ይለያል። የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞቹ እና ማሻሻያዎቹ የታክስ ሥርዓቱን ለማጣጣም እና የታክስ መሰረቱን ለማስፋት ያለመ ሲሆን፤ የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ደግሞ የታክስ አስተዳደርን ለማዘመን እና የታክስ ተገዥነት ለማሻሻል እና የታክስ ስወራንና ታክስ ማስቀረትን በመቀነስ የታክስ መሰረቱ በማስፋት የታክስ ገቢን ለማሳደግ ያለመ ነው።

በስትራቴጂው የሚከናወኑ ዋና ዋና የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች፡-

- የገቢ ግብር፤
- የኤክሳይስ ታክስ፤
- የጉምሩክ ቀረጥ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ እና
- የታክስ ማበረታቻ እና ነጻ፤

ይገኙበታል።

በስትራቴጂው የሚከናወኑ ዋና ዋና የታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች በርካታ ሲሆኑ፤ የታክስ አስተዳደር ስርዓቱን ዲጂታይዝ ማድረግ፣ የመረጃ አያያዝን ማሻሻል፣ የግብር ከፋይ አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል፣ የስጋት አስተዳደር ስርዓቱን መተግበርን ወዘተ በመተግበር የታክስ አስዳደር ስርዓቱን የማዘመን ሥራ መስራትን ያጠቃልላል።

በስትራቴጂው የትግበራ ዘመን ውስጥ በሚተገበሩ የታክስ ፖሊሲ እና በታክስ አስተዳደር ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች በስትራቴጂው የትግበራ ጊዜ መጨረሻ ላይ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ በቀደም ተከተል በ4 በመቶኛ እና በ2.9 መቶኛ በድምሩ በ6.9 በመቶኛ የማሳደግ ሥራ የሚሰራ ይሆናል።

እነዚህን ሁሉ ማሻሻያዎች በውጤታማነት እና በተቀናጀ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት የብሔራዊ የታክስ ሪፎርም ታስክ ፎርስ በማቋቋም ሥራ ጀምሯል። በሌላ በኩል ታስክ ፎርሱ ስራውን የሚደግፉ የታክስ ሪፎርም የቴክኒክ ኮሚቴ እና ዩኒቶች እንዲቋቋሙ አድርጓል።

በስትራቴጂው ውስጥ ቁልፍ የስኬት ምክንያቶች እና የአተገባበር ስጋቶች ተለይተዋል። የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣ የልማት አጋሮች እና የግብር ከፋዮች ድጋፍ እና እየተካሄደ ያለው

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች እንደ የስኬት ምክንያቶች ሆነው ተለይተዋል። የአተገባበሩ ስጋቶች ቀጠናዊና አለም አቀፋዊ ሁናቴዎች፣ በገቢዎች ባለስልጣን ያለው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ውስንነት፣ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት እና የግሉ ዘርፍ ኢኮኖሚ ጨምሮ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት የድጋፍ ውስንነት ናቸው።

# አባሪ

## አባሪ 1፡ ባለፉት ስድስት ዓመታት የተከናወኑ የታክስ ፖሊሲ ሪፎርሞች እና ማሻሻያዎች ማጠቃለያ

| | የፖሊሲ እርምጃዎች | ጊዜ አጠባበቅ | ተጽዕኖ | በገቢ ላይ ያላውን አንድምታ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የድንበር ፍራንኮ-ቫሉታ እና የታሪፍ ነፃነቶች | 2010 | ▪ የድንበር ተሻጋሪ ንግዱን ለማሳለጥ መንግስት በተመረጡ የድንበር አካባቢዎች የሚገኙ ነጋዴዎች በፍራንኮ ቫሉታ ዕቃዎች እንዲገቡ የሚፈቅድ ነበር፡፡<br>▪ ይሁን እንጂ አስተዳደራዊ አስቸጋሪነት እና ለመንግስት በየዓመቱ 4 ቢሊዮን ብር እንደሚያጣ ተረጋግጧል፡፡<br>▪ በተደረገው ጥናት መሰረት 2010 ዓ/ም ህጉ ተሽሯል፡፡ | ▪ የገቢን መጨመር |
| 2. | የተጨማሪ እሴት ታክስ መነሻ ማሻሻያ | 2010 | ▪ ከማሻሻያው በፊት ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ ዓመታዊ ሽያጭ ከብር 500 ሚሊዮን በላይ የነበረ ሲሆን፤ ላለፉት 15 ዓመታት ሳይሻሻል መቆየቱ በተለይ ከዋጋ ግሽበት አንጻር የሚጣጣም አለመሆኑ፡፡<br>▪ ዝቅተኛ ዓመታዊ ሽያጭ ያላቸው ወደ ስርዓቱ እንዲገቡ በማድረግ የታክስ አስተዳደር ጫና መፍጠሩ፤ እንዲሁም በርካቶች ወደ ስርዓቱ እንዲገቡ በማድረግ ለታክስ አስተዳደሩ ጫና መፍጠሩ፡፡<br>▪ በማሻሻያው የመመዝገቢያ ወሰኑ ወደ ብር 1 ሚሊዮን እንዲያድግ ተደርጓል፡፡ | ▪ ገቢን አይጨምርም አይቀንስም |
| 3. | የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ | 2011 | ▪ ከማሻሻያው በፊት በወኪሎች ተይዞ 100 በመቶ ለመንግስት ይገባ የነበረና የኢንቨስትመንት ከባቢን የሚጎዳ የነበረ መሆኑ፡፡<br>▪ በማሻሻያው የተቀናሽ ዋጋን ከ100 በመቶ ወደ 50 በመቶ እንዲሆን መደረጉ፤ በዚህም የታክስ ወኪሎች ከግዢያቸው 50 በመቶ ብቻ እንዲይዙ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፤ አቅራቢዎች ደግሞ የሚከፈለውን 50 በመቶ ተጨማሪ እሴት ታክስ በመሰብሰብ ለታክስ ባለስልጣን መላክ ይጠበቅባቸዋል፡፡ | ▪ ገቢን አይጨምርም አይቀንስም |
| 4. | የኤክሳይስ ታክስ ማሻሻያ | 2012 | ▪ የታክስ መሰረቱን እንዲሰፋ አድርጓል (የኤክሳይሳይዝ ታክስ ሲጣልባቸው ያልነበሩ ዕቃዎች ላይ ታክሱ እንዲጣል አድርጓል)፡፡<br>▪ በአገር ውስጥ ለሚመረቱ ዕቃዎች የታክስ ስርዓቱን ቀላል እና ተገማች እንዲሆን አድርጓል (የታክስ መሰረቱ ከማምረቻ | ▪ የገቢን መጨመር |

| | የፖሊሲ እርምጃዎች | ጊዜ አጠባበቅ | ተጽዕኖ | በገቢ ላይ ያላውን አንድምታ |
|---|---|---|---|---|
| | | | ወጪ ወደ ፋብሪካ መሸጫ ዋጋ እንዲቀየር አድርጓል)፡፡<br>▪ የኤክሳይዝ ታክስ ገቢ በሀገር ውስጥ ከሚመረቱ ዕቃዎች ሲጨምር ከውጭ ከሚገቡ ዕቃዎች እንዲቀንስ ያደረገ ሲሆን፤ በአጠቃላይ ገቢ ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡ | |
| 5. | የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ማሻሻያ | 2013 | ▪ የጉምሩክ ታሪፍ የመጣኔዎች ቁጥር ብዛት ከ 6 ወደ 5 በመቀነስ የጉምሩክ ስርዓቱ ቀላል አድርጓል፡፡<br>▪ በከፍተኛ ደረጃ ላልታለመለት ዓላማ ሲውል የነበረውን ሁለተኛው መደብ ሀ የጉምሩክ ታሪፍ እንዲቀር አድርጓል፡፡ | ▪ ገቢን አይጨምርም አይቀንስም |
| 6. | የሱር ታክስ ማሻሻያ | 2013 | ▪ የጉምሩክ ቀረጥ 15 በመቶ ወይም ከዚያ በታች ባለው ሁሉም ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያለውን ቀረጥ ተነስቷል፡፡<br>▪ በገቢ ዕቃዎች ላይ ያለውን የታክስ ጫና እንዲቀንስ በማድረግ፤ የኢኮኖሚ መዛባትን መቀነስ፡፡<br>▪ በአንጻሩ ለመንግስት የገቢ መቀነስን አስከትሏል፡፡ | ▪ የገቢን የመቀነስ |
| 7. | የታክስ ማበረታቻ አስተዳደርን በተማከለ አግባብ እንዲሚራ ማድረግ | ግንቦት 2013 | ▪ ከዚህ ቀደም የታክስ ማበረታቻ ከ35 በላይ በሆኑ የመንግሰት ተቋማት የሚሰጥ ነበር፡፡<br>▪ በግንቦት 2013 ዓ/ም መንግስት የታክስ ማበረታቻ አሰጣጡ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል እንዲሆን አድርጓል፡፡<br>▪ የታክስ ማበረታቻ አስተዳደሩ በተማከለ አግባብ እንዲሆን ማድረጉ አጠቃላይ አስተዳደር አሻሽሏል; | ▪ የገቢን መጨመር |
| 8. | የታክስ ማበረታቻዎችን ምክንያታዊ ማድረግ | 2014 | ▪ ማሻሻያው መንግስትን ከፍተኛ ገቢ የሚያሳጡ ነገርግን ኢንቨስትመንትን በማበረታታት ረገድ ውጤታማ ያልሆኑ ማበረታቻዎችን ማስቀረት (ባለሀብቶች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከቀረጥ ነፃ ፒክ አፕ መኪና ማስገባት ማስቀረትን ጨምሮ)፡፡ | ▪ የገቢን መጨመር |
| 9. | የማህበራዊ ደህንነት ቀረጥ | 2014 | ▪ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ሁሉም ምርቶች ላይ (በሲአይኤፍ ዋጋ ላይ) የ3 በመቶ ቀረጥ ይጥላል፡፡<br>▪ የሱር ታክስ በመነሳቱ ምክንያት ከሚታጣው ገቢ በላይ መጨመር፡፡ | ▪ ገቢን መጨመር |